
# የወላጅ መብቶች

## የሜሪላንድ የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ

*የጨቅላ ሕፃናት እና ሕፃናት የቅድሚያ ጣልቃ ገብ*
*እርዳታ፣ የቅድመ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ትምህርት*
*እና*
*የልዩ ፍላጎት ትምህርት*



**ጃንዋሪ 2021 የተሻሻለ**

**የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ/የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል**

**የወላጅ መብቶች**
**የሜሪላንድ የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ**
**የጨቅላ ሕፃናት እና ሕፃናት፣ የቅድመ ትምህርት፣ ልዩ ፍላጎት ትምህርት**
ጃንዋሪ 2021

© 2013 Maryland State Department of Education

ይህ ሰነድ ከዩ.ኤስ የትምህርት መምሪያ IDEA Part C Grant#H181A120124 እና IDEA Part B Grant #H027A012035A በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ፣ በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ (MSDE) የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ/የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል ዳብሮና ታትሞ የተዘጋጀ ነው፡፡ የቅጂ መብት 2013፣ የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ (MSDE)። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ ሆኖም ከ MSDE የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ/የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ። ሁሉም ሌሎች መብቶች በህግ የተጠበቁ ናቸው። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሔራዊ ማንነት፣ በሃይማኖት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ወይም በፆታ ዝንባሌ ላይ ተመስርቶ የሥራ ቅጥርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ወይም የፕሮግራሞች ተደራሽነት አቀራረብ ላይ አድሎ አያደርግም። የመምሪያ ፖሊሲዎችን ለተመለከቱ ጥያቄዎች የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ የስቴት አስተዳደር ምክትል ዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ፣ የፍትሃዊነት ማረጋገጫ እና ተገዢነት ቅርንጫፍን ያነጋግሩ፣ 200 West Baltimore Street, 6th floor, Baltimore, MD 21201-2595, 410-767- 0433, ፋክስ 410-767-0431, www.MarylandPublicSchools.org. በአካል ጉዳተኛ አሜሪካዊያን አዋጅ (Americans with Disabilities Act [ADA]) መሠረት ይህ ሰነድ፣ በተጠየቀ ጊዜ፣ በአማራጭ ቅርጸቶች ይገኛል። የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ/የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል በድምጽ (410) 767-7770 ወይም በፋክስ (410) 333-1571 ያናግሩ።

**Mohammed Choudhury**
የስቴት ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ

**Clarence C. Crawford**
ፕሬዝዳንት
የስቴት የትምህርት ቦርድ

**Carol A. Williamson, Ed.D.**
ዋና የትምህርት ሹም

**Marcella E. Franczkowski, M.S.**
የስቴት ረዳት ዋና ተቆጣጣሪ
የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ/የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል

**Larry Hogan**
አገረ ገዥ

Maryland State Department of Education
Division of Early Intervention/Special Education Services
200 West Baltimore Street
Baltimore, Maryland 21201
410-767-7770 (ስልክ)
410-333-1571 (ፋክስ)
http://www.marylandpublicschools.org

ይህ ሰነድ ከሜሪላንድ ስቴት ትምህርት መምሪያ፣ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል በሚቀጥሉት ቋንቋዎች ይገኛል፡ አማርኛ፣ አረብኛ፣ ቤንጋሊ፣ በርማኛ፣ ቻይንኛ፣ ዳሪ)፣ ፈረንሳይኛ፣ ጉጃራቲ፣ ሃይቲ፣ ዕብራይስጥ፣ ሂንዲ፣ ጃፓንኛ፣ ኮሪያኛ፣ ኔፓሊኛ፣ ፓሽቶ፣ ፖርቱጋልኛ፣ ሩሲያኛ፣ ስፓኒሽ፣ ታጋሎግ፣ ቱርክኛ፣ ኡርዱ እና ቬትናምኛ።

# ማውጫ


**የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ....1**

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ....1**

**ኢ-ሜይል....2**

**የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ....2**

ማስታወቂያ:....2

የጽሑፍ ማስታወቂያ ይዘት:....3

**ስምምነት....3**

**የወላጅ ስምምነት:....3**

IEP – ክፍል B....4

የመጀመሪያውን ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ስምምነት:....4

በስቴቱ ጥበቃ ስር ላሉ ሕጻናት የመጀመሪያ ግምገማ ልዩ ደንቦች:....4

ለአገልግሎቶች የወላጅ ስምምነት:....4

ለአገልግሎቶች የተሰጠን የወላጅ ስምምነት መሻር:....5

ለ IFSP ዳግም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት ለሕጻናትና ወጣቶች ብቻ:....5

የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት የተደረጉ ምክንያታዊ ጥረቶችን መመዝገብ:....5

ለስምምነት መሟላት ያለባቸው ሌሎች ነጥቦች:....6

IFSP – ክፍል C....6

በ IFSP በኩል አገልግሎቶችን ለማግኘት የወላጅ ስምምነት:....6

ወላጆች አገልግሎቶችን ያለመቀበል መብትም አላቸው:....7

ለተጨማሪ ምዘናዎች ወይም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት:....7

**በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ....7**

ትርጓሜዎች:....8

የሕዝብ ኤጀንሲ መመዘኛዎች:....8

በሕዝብ ወጪ ከሚደረግ ግምገማ ጋር በተያያዘ የወላጅ መብት:....8

በወላጅ አነሳሽነት የሚደረግ ግምገማ:....8

ግምገማ እንዲደረግ በአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) የሚቀርብ ጥያቄ:....9

**ምትክ ወላጆች....9**

ምትክ ወላጅ ለመሆን ያሉ መስፈርቶች:....9

**የመረጃ ሚስጥራዊነት....9**

ትርጓሜዎች:....10

ከለላዎች:....10

ስምምነት:....10

የመጎብኘት/የመመልከት መብቶች:....11

የመጎብኘት/የመመልከት ሪኮርድ:....12

በወላጅ ጥያቄ መሠረት ሪኮርዶችን ማስተካከል:....12

መረጃን የመደምሰስ አሰራር ሂደቶች:....13

የልጆች መብቶች:....13

የዲሲፕሊን እርምጃን የተመለከቱ መረጃዎች:....13

**የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ዲሲፕሊን ..... 14**

ትርጓሜዎች: ..... 14

የትምህርት ቤት ባልደረቦች ሥልጣን: ..... 14

አገልግሎቶች: ..... 15

የባህሪ መገለጫዎች መወሰኛ ግምገማ ..... 15

ልዩ ሁኔታዎች: ..... 16

የምደባ ለውጥ: ..... 17

የሥነ-ምግባር እርምጃ ይግባኝ/አቤቱታ: ..... 17

ልጁ ገና ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ..... 18

ወደ ሕግ አስከባሪና የዳኝነት ባለሥልጣናት መተላለፍና የሚወሰድ እርምጃ ..... 19

**ወላጆች በተናጠል ልጃቸውን የግል ትምህርት ቤት ..... 19**

በወጪዎች ማካካሻ ላይ ገደብ: ..... 19

**የወላጅነት መብትን አካለ መጠን ..... 20**

**አለመግባባቶችን ስለመፍታት ..... 21**

ግልግል: ..... 21

ግልግልን ለማበረታታት መገናኘት: ..... 22

በስቴት አቤቱታና በፍትህ ሂደት አቤቱታ መካከል ያለው ልዩነት: ..... 22

የስቴት አቤቱታ: ..... 23

የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት: ..... 24

የፍትህ ሂደት አካል የሆነ የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት: ..... 24

የፍትህ ሂደት አቤቱታ: ..... 24

የፍትህ ሂደቱ አቤቱታ ይዞታ: ..... 25

ለፍትህ ሂደት አቤቱታው የሚሰጥ ምላሽ: ..... 25

የማስታወቂያ ብቃት: ..... 26

በፍትህ ሂደቶች ጊዜ የልጁ ሁኔታ/ቦታ: ..... 26

ችግሩን የመፍታት ሂደት: ..... 27

የችግር መፍቻ የ 30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች: ..... 27

የችግሩን መፍትሔ ስምምነት: ..... 28

የፍትህ ሂደት ችሎት: ..... 28

የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ): ..... 28

የፍትህ ሂደት አቤቱታ ርእስ: ..... 29

የይግባኝ መብቶች: ..... 29

ተጨማሪ መረጃን ይፋ ማድረግ: ..... 29

የወላጅ መብቶች: ..... 29

የይግባኝ ውሳኔ: ..... 29

ለብቻው የተለየ የፍትህ ሂደት አቤቱታ: ..... 30

የጊዜ ሰሌዳዎችና የችሎት አመቺነት: ..... 30

የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት (IEP ብቻ): ..... 30

የፍትህ ሂደት ችሎት ውሳኔ: ..... 30

የፍርድ መጨረሻነት: ..... 31

ይግባኝ: ........ 31

**የጠበቆች ክፍያ........ 31**

**የIDEA የአለመግባባት ፍቺ አሠራሮች ማወዳደሪያ ሠንጠረዥ........ 33**

# የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ

## 34 C.F.R. § 300.504 እና § 303.421 and § 303.404

**የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ በቀላሉ ለመረዳት በሚቻልበት መንገድና በትውልድ ቋንቋዎ የተጻፈ ሲሆን የመብቶችዎን ሙሉ ማብራሪያ ያካትታል። ይህ የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ በፌዴራል አካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ ስር፣ ለአካል ጉዳተኛ ልጆች እና ቤተሰቦች ተፈፃሚ ይሆናል።**

በዚህ ሰነድ ውስጥ የተካተቱት ከለላዎች አካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA)፣ 20 U.S.C. §1400 *et seq*፣ በፌዴራል መመሪያዎች ሕግ (CFR), 34 C.F.R. § 300.1 *et. Seq.*. (IEP) *እና* 34 C.F.R. § 303.1 *et. seq.* (IFSP) እና ሌሎችም እና በሜሪላንድ ደንቦች ኮድ ወይም COMAR ውስጥ በሚገኙት በሚከተሉት አንቀጾች አማካኝነት የተመሠረተ ነው፡ COMAR 13A.05.01, COMAR 13A.08.03, እና COMAR 13A.13.01. እያንዳንዱ የሕዝብ ኤጀንሲ የIDEA መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሥርዓት ከለላዎችን ይመሠርታል፣ ይጠብቃል እንዲሁም ሥራ ላይ ያውላል። ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ ይህ ማስታወቂያ ለክፍል B IEPን እና ለክፍል C IFSPን በማመልከት ለ IDEA ክፍል B ወይም ለክፍል C ተፈፃሚነት ያላቸውን ክፍሎች ያሳያል።

በ IFSP በኩል አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት እና ቤተሰቦች፣ ወላጆች በሚከተሉት ሂደቶች ላይ የሥርዓት ከለላዎች ቅጂ ይቀበላሉ፡

- የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎት ሰጪው የልጁን ግምገማ ወይም ምደባ፣ ወይም የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን ለልጁ እና ለልጁ ቤተሰብ ማቅረብ ለመጀመር ወይም ለመለወጥ ሃሳብ ሲያቀርብ ወይም እንደማይቀበል በሚገልጽበት ጊዜ ጨምሮ፣ ከቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ጋር፣
- በክፍል C ስር አንድ ልጅ ለቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ሲመራ፤ ወይም
- የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ለማቅረብ ስምምነት በሚቀበሉበት ጊዜ ከስቴቱ የክፍያ ፖሊሲዎች ቅጅ ጋር።

በ IEP በኩል አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት፣ የሥርዓት ከለላዎች ሰነድ ቅጂ ለወላጆች በዓመት አንድ ጊዜ ይሰጣል፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ወቅት የሕዝብ ኤጀንሲ ለወላጆች ሌላ የሰነዱን ቅጂ ይሰጣል፡

- መጀመሪያ በሚመሩበት ወቅት ወይም የግምገማ ጥያቄ በወላጅ ሲቀርብ፤
- በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ የመጀመሪያው የስቴት አቤቱታ በጽሁፍ በቀረበበት ጊዜ፤
- በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ የመጀመሪያ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በቀረበበት ጊዜ፤
- የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ በተወሰነ ጊዜ፤ እና
- በወላጅ ሲጠየቅ።

አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ድረ ገጽ ካለው ወቅታዊ የሆነውን የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ ቅጂ በኢንተርኔት ድረ ገጹ ላይ ሊያወጣ ይችላል።

የሥርዓት ከለላ ሰነድ የወላጆችን መብቶች ሙሉ ማብራሪያ የሚያካትት ሲሆን በቀላሉ ለመረዳት በሚቻልበት መንገድና ይህን ማድረግ በግልጽ የማይቻል ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በወላጅ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተጻፈ ነው። የአፍ መፍቻ ቋንቋው ወይም ሌላው የመግባቢያ ዘዴ በጽሑፍ የሚገለጽ ካልሆነ የሕዝብ ኤጀንሲው የሥርዓት ከለላዎቹ በቃል ወይም በሌላ አመቺ መንገድ ወደ ወላጁ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴ መተርጎም ይኖርበታል። የሕዝብ ኤጀንሲው ማስታወቂያው በአግባቡ መተርጎሙንና ወላጆችም የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያውን ይዘትን በአግባቡ የተረዱት መሆኑን ለማረጋገጥ የጽሁፍ ማስረጃ ማስቀመጥ አለበት።

# የአፍ መፍቻ ቋንቋ

**IEP እና IFSP**

**34 C.F.R. § 300.612, § 300.29, § 303.421, እና § 303.25**

## ወላጆች እነሱ በሚረዱት ቋንቋ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው ጥቂት ከሆነ ግለሰብ ጋር በሚጠቀሙበት ጊዜ የትውልድ ቋንቋ ማለት የሚከተሉትን ነው፡

- ይህ ሰው ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምበት ቋንቋ ወይም ልጅም ከሆነ የልጁ ወላጆች ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙበት ቋንቋ፣
- ከልጁ ጋር በቀጥታ በሚገናኙበት ጊዜ ሁሉ (የልጁን ግምገማም ጨምሮ) ልጁ በቤቱ ውስጥ ወይም በሚማርበት አካባቢ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምበት ቋንቋ።

መስማት የሚሳነው ወይም አይነ ስውር የሆነ ሰው፣ ወይም የጽሑፍ ቋንቋ የሌለው ሰው ከሆነ የመግባቢያ ዘዴው ይህ ሰው ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምበት ዘዴ መሆን አለበት (መስማት የሚሳናቸው ሰዎች የሚጠቀሙበት የምልክት ቋንቋ፣ የአይነ ስውራን ሥርዓተ ጽሕፈት ወይም የቃል ንግግር)።

ወላጆች የልጃቸውን የተሞላ አይኤፍኤስፒ ወይም አይኢፒ ወደ መጀመሪያ ቋንቋቸው እንዲተረጎም መጠየቅ ይችላሉ። በወላጆች የሚነገረው ቋንቋ በአካባቢው ካለው የትምህርት ስርዓት ባለው የተማሪው ብዛት ውስጥ ከ (1%) በላይ የሚነገር ከሆነ፣ የሚመለከታቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለወላጆቹ የተተረጎመውን ዶክመንት ከተጠየቀበት ቀን በ 30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው። ይህ የአንድ ፐርሰንት ትርጉም መጠይቅ በዚህ ዶክመንት የግልግል ክፍል ውስጥም ተጠቅሷል።

# ኢ-ሜይል

## <u>IEP እና IFSP</u> 34 C.F.R. § 300.505

**አማራጩ ካለ ወላጆች ማስታወቂያዎች በኢሜል እንዲደርሳቸው ማድረግ ይችላሉ።** አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ወላጆች ሰነዶች በኢሜይል እንዲደርሳቸው አማራጭ የሚሰጥ ከሆነ የሚከተሉት በኢሜይል እንዲደርስዎት ማድረግ ይችላሉ፡

- የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ፤
- የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ፤ <u>እና</u>
- የፍትህ ሂደትን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች።

# የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ

## <u>IEP እና IFSP</u>

## 34 C.F.R. §§ 300.503 እና 303.421

***ወላጆች አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ የልጃቸውን የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ወይም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች በተመለከተ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው።***

## *ማስታወቂያ፡*

አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ የሚከተሉትን ከማድረጉ ተገቢውን ጊዜ ያህል ቀድሞ ለወላጆች የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡

- የአንድን ልጅ ማንነት መለያ፤
- ግምገማ፤
- ትምህርታዊ መርሀ-ግብር፤
- የልጁ ትምህርታዊ ምደባ
- ለልጁ የሚሆን አግባብ ያለው ነጻ ሕዝባዊ ትምህርት (FAPE) አቅርቦት ወይም
- ለልጁና ለልጁ ቤተሰብ አስቀድሞ በIFSP በኩል የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች አቅርቦት፣ ወይም
- ለልጁ በ IEP የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች አቅርቦት

አንድ የጽሑፍ ማስታወቂያ የወላጅ ፍቃድ ከሚያስፈልገው እርምጃ ጋር የተያያዘ ከሆነ የሕዝብ ኤጀንሲው የጽሑፍ ማስታወቂያ አብሮ አንድ ላይ ሊሰጥ ይችላል።

# የጽሑፍ ማስታወቂያ ይዘት፡

በ IFSP በኩል አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት እና ቤተሰቦች የጽሁፍ ማስታወቂያው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡

- የቀረበውን ወይም ተቀባይነት ያላገኘውን እርምጃ መግለጽ፤
- እርምጃው የተወሰደበትን ምክንያት፤ እና
- የሥርዓት ከለላዎችን ማካተት አለበት፡፡

በ IEP በኩል አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት የጽሑፍ ማስታወቂያው የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡

- የሕዝብ ኤጀንሲው ያነሳሳው/ያነሳሳቸው ወይም ውድቅ ያደረገው/ያደረጋቸው ድርጊት/ቶች ማብራሪያ መስጠት፣
- የሕዝብ ኤጀንሲው ድርጊቱን/ድርጊቶቹን ለመፈጸም ወይም ለመቃወም ምን እንዳነሳሳው የሚገልጽ ማብራሪያ፣
- የሕዝብ ኤጀንሲው ድርጊቱን/ድርጊቶቹን ለመፈጸም ወይም ለመቃወም የወሰነበትን እያንዳንዱን የግምገማ ሂደት፣ ምዘና፣ መዝገብ ወይም ሪፖርት የሚያብራራ መግለጫ፣
- ወላጆች IDEA ውስጥ በሚገኙት የሥርዓት ከለላ ድንጋጌዎች መሠረት መብቶች እንዳላቸው የሚገልጽ መግለጫ፤
- የሕዝብ ኤጀንሲው የሚፈጽመው ወይም የሚቃወመው ድርጊት ለግምገማ የሚተላለፍ የመጀመሪያ ድርጊት ካልሆነ ወላጆች የሥርዓት ከለላዎች ቅጂ የሚያገኙበትን መንገድ መናገር፣
- ወላጆች IDEA ን ለመረዳት እርዳታ የሚያገኙባቸውን ምንጮች ማካተት፣
- የልጁ የግል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ያያቸውን አማራጮች ማብራራትና ምርጫዎቹ ውድቅ ተደርገው የተተውበትን ምክንያቶች መንገር፤ <u>እ</u> <u>ንዲሁም</u>
- የሕዝብ ኤጀንሲው ድርጊቱን ለመፈጸም ወይም ለመቃወም የተጠቀመባቸውን ምክንያቶች ማብራሪያ ማቅረብ።

# ስምምነት

**<u>IEP እና IFSP</u>**

**34 C.F.R. § 300.300 እና 34 C.F.R. § 303.420**

# የወላጅ ስምምነት፡

**የሕዝብ ኤጀንሲ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ከመስጠት በፊት ለቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ እና ለልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች አንድን ልጅ ከመገምገሙ በፊት ለሁለቱም የወላጅ ስምምነት ማግኘት አለበት። ወላጆች በማንኛውም ጊዜ የሰጡትን ስምምነት የመሻር መብት አላቸው። ለግምገማ ስምምነት የተወሰኑ በልዩ ሁኔታ ከግምት የሚገቡ ጉዳዮች አሉ።**

ስምምነት ማለት ወላጆች፡

- ስምምነቱ ስለሚመለከታቸው ተግባራት ተገቢ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወይም በሌላ የግንኙነት መንገድ ሙሉ በሙሉ ሲነገራቸው፤
- ግንዛቤ ሲኖራቸው እና ስምምነታቸው የሚመለከታቸውን ተግባራት እንዲከናወኑ በጽሑፍ ስምምነታቸው ሲገልጹ እና ስምምነቱም ያን ተግባራት ሲገልጽ እንዲሁም የሚለቀቁ መዝገቦቹ (ካሉ) እና

  ለማን እንደሚለቀቁ ሲገለጽ፤ እና
- ስምምነትን መስጠት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና በማንኛውም ሰዓት ሊሻር እንደሚችል ሲገነዘቡ ነው።

ወላጆች ስምምነታቸውን ከሻሩ፣ የሕዝብ ኤጀንሲ ስምምነቱን በተቀበለበት ጊዜ እና ስምምነቱ በተሻረበት መካከል ባለው ጊዜ የተከናወኑ ተግባራትን አይሰርዝም።

ወላጅ ልጃቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግልቶች ከተሰጠው በኋላ ልጃቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን ከመውሰድ ስምምነቱን በጽሑፍ ከሰረዘ፣ ስምምነቱ ከመሰረዙ የተነሳ የሕዝብ ኤጀንሲ ልጁ የወሰደውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በተመለከተ መረጃውን ለማስወገድ የልጁን የትምህርት ውጤቶችን ለማስተካከል አይገደድም።

# IEP – ክፍል B

## የመጀመሪያውን ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ስምምነት፡

አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ለቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ እና ለልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የአንድን ልጅ ብቁነት ለመወሰን የመጀመሪያ ግምገማ ከማድረጉ በፊት እና ለመጀመሪያ ጊዜ የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ከመስጠቱ በፊት የወላጅ ስምምነት ማግኘት አለበት።[1] አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ አንድ ልጅ ለልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎች ብቁ መሆኑን ለመወሰን የመጀመሪያ ግምገማ ማድረግ ከመቻሉ በፊት የሕዝብ ኤጀንሲው የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡

- ለወላጆች ስለ ታቀደው እርምጃ በጽሑፍ የቅድሚያ ማስታወቂያ መስጠት፤ እንዲሁም
- የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ከማካሄዱ በፊት ከወላጅ በመረጃ የታገዘ ስምምነት ማግኘት፤ እና
- ከቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ በተጨማሪ የሥርዓት ከለላዎች ማስታወቂያ ቅጅ ለወላጅ መስጠት አለበት።

የሕዝብ ኤጀንሲው አንድ ልጅ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚፈልግ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ነው ብሎ ለመወሰን የመጀመሪያ ግምገማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን በመረጃ የታገዘ ስምምነት ለማግኘት ተገቢ ጥረት ማድረግ አለበት። በመንግሥት ትምህርት ቤት የተመዘገበ ወይም በመንግሥት ትምህርት ቤት ለመመዝገብ የሚፈልግ ልጅ ወላጅ ለመጀመሪያው ግምገማ ስምምነት ካልሰጠ ወይም ወላጁ ስምምነቱን እንዲሰጥ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ መስጠት ካልቻለ የሕዝብ ኤጀንሲው፣ እንደ ግልግል ወይም የፍትህ ሂደት አቤቱታ ያሉ እዚህ ውስጥ የበለጠ የተብራሩትን የሥርዓት ከለላዎችን በመጠቀም የልጁን የመጀመሪያ ግምገማ ሊያከናውን ይችላል፣ ነገር ግን ይህን ማድረግ አይጠበቅበትም።[2]

በቤት ውስጥ የሚማር ወይም በራሳቸው በወላጆቹ ወጪ በግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ልጅ አንድ ወላጅ ለመጀመሪያው ግምገማ ወይም ለዳግም ምዘና ስምምነት ካልሰጠ ወይም ወላጁ ስምምነቱን እንዲሰጥ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ መስጠት ካልቻለ የሕዝቡ ኤጀንሲው ከላይ የተገለጹትን የስምምነት መሻሪያ ሂደቶች ሊጠቀም አይችልም።[3]

አንድ ወላጅ ለመጀመሪያ ግምገማ ስምምነት ሰጠ ማለት የሕዝብ ኤጀንሲው የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለልጁ መስጠት እንዲጀምርም ስምምነት ሰጠ ማለት አይደለም።

## በስቴቱ ጥበቃ ስር ላሉ ሕጻናት የመጀመሪያ ግምገማ ልዩ ደንቦች፡

አንድ ልጅ በግዛቱ ጥበቃ ስር የሚገኝ ከሆነ እና ከወላጆቹ ጋር የማይኖር ከሆነ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ የህዝብ ኤጀንሲው ልጁ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ መሆንና አለመሆኑን ለመወሰን የመጀመሪያ ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ስምምነት አያስፈልገውም፡

- ምክንያታዊ የሆነ ጥረት አድርጎ ቢሆንም የልጁን ወላጆች ማግኘት ካልቻለ፤
- በስቴቱ ህግ መሰረት የወላጆቹ መብት ተቋርጦ ከሆነ፤ ወይም
- አንድ ዳኛ የትምህርት ጉዳዮች ላይ መወሰንን እና ለመጀመሪያ ጊዜ ግምገማ ስምምነት የመስጠት መብት ከወላጅ ሌላ ለሆነ ግለሰብ አስተላልፎ ከሆነ፡፡

## ለአገልግሎቶች የወላጅ ስምምነት፡

የመንግሥት ኤጀንሲ ለአንድ ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ከመስጠቱ በፊት

(1) 34 CFR § 300.300(a).
(2) 34 CFR § 300.300(a)(3)(i).
(3) 34 CFR § 300.300(d)(4)(i-ii).

በመረጃ የታገዘ ስምምነት ማግኘት አለበት። ወላጆቹ የሚከተሉትን ካደረጉ የሕዝብ ኤጀንሲው የልጁ ወላጆች ስምምነት ሳይሰጡ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለልጁ ሊሰጡ እንደሚችሉ የሚያመለክት ውሳኔን ወይም ስምምነት ለማግኘት የግልግል ወይም የፍትህ ሂደቶችን መጠቀም <u>የለበትም</u>፡

- ልጃቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ስምምነት አልሰጥም ካሉ፣ ወይም
- ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ስምምነት እንዲሰጡ ተጠይቀው መልስ ሳይሰጡ ከቀሩ።

ወላጆች ልጃቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያገኝ ስምምነት አልሰጥም ካሉ፣ ወይም ወላጆች ስምምነት እንዲሰጡ ተጠይቀው መልስ ሳይሰጡ ከቀሩ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው፡

- የነጻ ተገቢ ሕዝባዊ ትምህርት (FAPE) ለልጃቸው እንዲኖር ማድረግ ያለባቸውን ግዴታ ሕግ አልጣሱም፤ <u>እንዲሁም</u>
- ለልጃቸው ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ የማድረግ ወይም ለልጃቸው IEP የማዳበር ግዴታ የለበትም።

# ለአገልግሎቶች የተሰጠን የወላጅ ስምምነት መሻር፡

የአንድ ልጅ ወላጅ የሕዝብ ኤጀንሲው የመጀመሪያ ልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማቅረብ ከጀመረ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች አቅርቦት ቀጣይነት የሰጠውን ስምምነት በጽሑፍ ከሰረዘ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው፡

- ስምምነት ስለተሰረዘ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ልጁ እንዳገኘ የሚያሳይ ማንኛውንም ሰነድ ከመዝገብ የመሰረዝ ግዴታ የለበትም፤
- ለልጁ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መስጠት መቀጠል የለበትም ግን የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገግልግሎቶች ማቅረብ ከማቆሙ በፊት፣ ወላጅ በጽሑፍ ሁሉም የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲቆሙ ያቀረበው ጥያቄ እንደደረሰው በቅድሚያ በጽሑፍ ማስታወቂያ ለወላጅ መስጠት አለበት፤
- ግልግል ወይም የፍትሕ ሂደት ተጠቅሞ ስምምነትን ማግኘት ወይም አገልግሎቶቹ ለልጁ እንዲሰጡ ማስፈረድ አይችልም፤
- ለልጁ ከዚህ በኋላ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መስጠት ስላልቻለ FAPE የመስጠቱን ግዴታ አላሟላም ተብሎ ቅጣት አይደርስበትም፣ እንዲሁም
- ከአሁን በኋላ ለልጁ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለማቅረብ የIEP ቡድን ስብሰባ መጥራት ወይም ለልጁ IEP ማዘጋጀት አይጠበቅበትም።

ስምምነትን መሻር የሕዝብ ኤጀንሲው ስምምነቱ በደረሰውና ስምምነቱ እስከተሻረበት ድረስ ባለው ጊዜ ላይ የተከሰተ ድርጊትን አይሰርዝም።

# ለ IFSP ዳግም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት ለሕጻናትና ወጣቶች ብቻ፡

የሕዝብ እጀንሲው ለልጁ ዳግም ግምገማ ከማድረጉ በፊት በመረጃ የታገዘ ስምምነት ማግኘት አለበት፣ ካልሆነ ግን ኤጄንሲው የሚከተለውን ማሳየት አለበት፡

- ለዳግም ግምገማ የወላጅን ስምምነት ለማግኘት ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰዱን፤ <u>እ ና</u>
- ወላጅ ምላሽ አለመስጠቱን።

ለአዲስ ግምገማ ወላጅ ስምምነት ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የሕዝብ ኤጄንሲው ምንም እንኳን ግዴታው ባይሆንም፣ የወላጅን እምቢታ በመግታት ስምምነት ለማግኘት የግልግል ዳኝነት ወይም የፍትህ ችሎት ሂደቶችን በመከተል የወላጅን እምቢታ ማስወገድ ይችላል። በመጀመሪያ ጊዜ በነበረው ግምገማ እንደነበረው፣ የሕዝብ ኤጄንሲ አዲስ ግምገማ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ከተቋረጠ፣ በ IDEA ሥር ያለውን ሕግ መጣስ የለበትም።

# የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት የተደረጉ ምክንያታዊ ጥረቶችን መመዝገብ፡

አንድ የሕዝብ ኤጄንሲ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ ዳግም ግምገማ ለማድረግና በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያሉ ልጆችን የመጀመሪያ ግምገማ ለማድረግ የወላጆች ስምምነት ለማግኘት ያደረጋቸውን ተገቢ ጥረቶች መዝግቦ በሰነድ መያዝ አለበት።
ሰነዱ የሕዝብ ኤጄንሲው የወላጅ ስምምነት ለማግኘት ያደረጋቸውን የሚከተሉት ዓይነት ሙከራዎች ሪኮርድ ማካተት

አለበት፡

- በስልክ ለማግኘት የተደወለባቸው ወይም የተሞከረባቸው ዝርዝር ሬኮርዶችና የስልክ ጥሪዎቹ ውጤቶች፤
- ለወላጆች የተላኩ የደብዳቤ ግልባጮችና ምንም ዓይነት ምላሾች፣ እንዲሁም
- የወላጅ ቤት ወይም ሥራ ላይ የተደረጉ ጉብኝቶች የዝርዝር ሬኮርዶችና ውጤታቸው።

# ለስምምነት መሟላት ያለባቸው ሌሎች ነጥቦች፡

የወላጅ ስምምነት በሕዝብ ኤጀንሲ ፊት መቅረብ አስፈላጊ ያልሆነባቸው ጊዜዎች፡

- *የልጅዎን ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ ለማድረግ የነበረ መረጃን ሲገመግሙ፣ ወይም*
- *ለሁሉም ልጆች የሚሰጥ ፈተና ወይም ሌላ ግምገማ ለልጅዎ ሲሰጥ፣ ፈተናው ወይም ግምገማው ከመሰጠቱ በፊት ከልጆቹ ወላጆች ሁሉ ስምምነት የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር።*

የሕዝብ ኤጀንሲው ወላጅ ለአንድ አገልግሎት ወይም ድርጊት ስምምነት አልሰጥም ያለበትን እምቢታ ተጠቅሞ ወላጁን ወይም ልጁን ከሌላ አገልግሎት፣ ጥቅማጥቅም ወይም ተግባራት መከልከል አይችልም።

አንድ ወላጅ ልጃቸውን በቤት ውስጥ የሚያስተምሩ ወይም በራሳቸው ወጪ በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ቢያስመዘግቡ፣ የሚከተሉት ከተከሰቱ የሕዝብ ኤጀንሲው በሽምግልና የሚደረግ ግልግልን ወይም የፍትህ ሂደትን ተጠቅሞ የልጁን ብቃት መገምገም አይችልም እንዲሁም ልጁ በ 34 C.F.R. §§ 300.132-300.144 ስር ተገቢ አገልግሎቶች እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ የለበትም፡

- *ወላጁ ልጁ የመጀመሪያ ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ እንዲያገኝ ስምምነት አልሰጠም፣ ወይም*
- *ወላጁ ስምምነት እንዲሰጥ ተጠይቆ መልስ ካልሰጠ።*

አይዲኢኤ (IDEA) የወላጅ ስምምነት ከሚጠይቅባቸው (የመጀመሪያ ግምገማ፣ የመጀመሪያ የአገልግሎቶች አቅርቦት፣ እና የድጋሚ ግምገማ) ተግባራት ውጪ፣ የሜሪላንድ ህግ የሚጠይቀው የአይኢፒ (IEP )ቡድን የሚከተሉትን ለማድረግ ካቀደ የወላጅን የጽሁፍ ስምምነት ማግኘት አለበት፥

- *ወደሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ክሬዲት የማይሰጥ የአማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ላይ ህጻኑን ማስመዝገብ፤*
- *ከግዛቱ የአማራጭ ሥርዓተ ትምህርት ጋር የተጣጣመውን የአማራጭ ትምህርት ግምገማን ህጻኑን ማስታወቅ፤ ወይም*
- COMAR 13A.08.04.05ላይ እንደተገለጸው የህጻኑን ጸባይ ለማስተካከል ግደባን ወይም ተገልሎ መቆየትን በአይኢፒው (IEP) ላይ ማካተት።

ከላይ ለተጠቀሱት ተግባራት ወላጁ የጽሁፍ ስምምነት ካላቀረበ፣ የአይኢፒ (IEP) ቡድኑ ለወላጅ የጽሁፍ የስምምነት መብታቸውን የሚገልጽ ከአይኢፒ( IEP) ቡድን ስብሰባ ከአምስት (5) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መላክ አለባቸው፤ ይህም የሚከተሉትን ለማስታወቅ ነው፡

- *ወላጅ የተጠቀሱትን ተግባራትን በተመለከተ ለመስማማትም ሆነ ላለመስማማት መብት እንዳለው፤ እና*
- ከአይኢፒ (IEP) ቡድን ስብሰባ በሁዋላ ባሉት አስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ ወላጅ የመስማማት ወይም ያለመስማማት ደብዳቤ ካላቀረበ፣ የአይኢፒ (IEP) ቡድኑ የተጠቀሱትን ተግባራት ስራ ላይ ያውላል።

ከላይ ለተጠቀሱት ማናቸውም እርምጃዎች ወላጅ ስምምነት ለምስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የህዝብ ኤጀንሲው ጉዳዩን ለመፍታት በትምህርት አንቀጽ §8-413 (ግልግል ወይም የፍትህ ችሎት ሂደት) የተቀመጠውን የእክል አፈታት አማራጮችን ሊጠቀም ይችላል።

# IFSP – ክፍል C
# በ IFSP በኩል አገልግሎቶችን ለማግኘት የወላጅ ስምምነት፡

የሚከተሉት ከመደረጋቸው በፊት ወላጅ የተነገራቸውን ስምምነት በጽሑፍ መስጠት አለበት፡

- ሁሉም የመለያ መንገዶች፣ ግምገማዎች፣ እና የልጁ እና የወላጁ የዳሰሳ ጥናቶች
- አስቀድሞ እርዳታ የማድረግ አገልጎቶችን መስጠት እና ተጨማሪ የዳሰሳ ጥናቶች መጀመር
- በጽሑፍ ስምምነት ካልተሰጠ፣ የአከባቢው የአመራሪ ኤጄንሲ ወላጅ የሚከተለው እንዲያደርግ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፤
    - የግምገማው እና የዳሰሳ ጥናቱን ባሕርያትን በተመለከተ ወይም ስለሚሰጡት አገልግሎቶች ብቁ ግንዛቤ እንዳላቸው ማረጋገጥ
    - በጽሑፍ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር፣ ልጁ ግምገማ ወይም የዳሰሳ ጥናት ወይም አገልግልቶችን እንደማያገኝ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ

# ወላጆች አገልግሎቶችን ያለመቀበል መብትም አላቸው፡

የአንድ ብቁ ልጅ ወላጅ ማናቸውንም የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች እርሳቸው፣ ልጃቸው ወይም ሌላ የቤተሰብ አባላት መቀበል ወይም አለመቀበላቸውን መወሰን ይችላሉ፣ ይህንንም አገልግሎት መጀመሪያ ተቀብለው በኋላ አልፈልግም ቢሉ ሌሎች የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን አያስተጓጉሉም። ወላጅ ዕድሜው ሶስት ወይም ከዛ በላይ ለሆነው ልጅ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች በተራዘመ IFSP አማካኝነት መቀጠል ቢፈልግ፣ የትምህርት ክፍል መካተት አለበት። ወላጅ የትምህርት ክፍሉን ካልፈለገ፣ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቃት የለውም።

# ለተጨማሪ ምዘናዎች ወይም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት፡

የሕዝብ ኤጀንሲው አዲስ የግል ግምገማዎች ለልጁ ከማካሄዱ በፊት፣ የሕዝብ ኤጀንሲው የሚከተሉትን በግልጽ ካላሳየ በስተቀር በመረጃ የታገዘ ስምምነት ማግኘት አለበት። ወላጅ ስምምነቱን ካልሰጠ፣ የሚመራው ኤጄንሲ ወላጆች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡

- በልጁ ላይ ሊደረግ የቀረበው የግመገማውን እና የዳሰሳውን ጠባይ በትክክል መረዳታቸውን ማወቅ፤ እና
- ስምምነት ካልተሰጠ በስተቀር ልጁ ግምገማ እና የዳሰሳ ጥናት ሊወሰድበት እንደማይችል መረዳታቸውን

ተጨማሪ ግምገማዎች ወይም ምዘናዎች ለማድረግ ወላጆች ስምምነት አልሰጥም ካሉ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት ችሎትን ተጠቅሞ የወላጆችን እምቢታ ማስሻር አይችልም፡፡

# በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ

**IEP ብቻ**

**34 C.F.R. § 300.502**

## አንድ ወላጅ የሕዝብ ኤጀንሲ በፈጸመው ግምገማ የማይስማማ ከሆነ፣ ወላጁ ለሕዝብ ኤጀንሲው በማይሠራ

**ሰው ልጁን የማስገምገም መብት አለው።**

**በክፍል B ስር ያሉ የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጆች ብቻ ገለልተኛ ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው።**

# ትርጓሜዎች፡

- በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ ማለት፣ ለልጁ ትምህርት ኃላፊነት ላለበት የሕዝብ ኤጀንሲ ተቀጥሮ በማይሠራ፣ ሌላ ብቁ ሠራተኛ የሚደረጉ የግምገማ ሂደቶች ናቸው፤ እንዲሁም
- የሕዝብ ወጪ ማለት የሕዝብ ኤጀንሲው የግምገማ ወጪውን በሙሉ ይከፍላል ወይም ግምገማው የሚሰጠው በወላጆች ወጪ እንዳልሆነ ያረጋግጣል።

ከዚህ በታች ባሉት ሂደቶች መሠረት ወላጆች ለልጃቸው በ IDEA ሥር ለልጃቸው በግል የሚሰጥ የትምህርት ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የሕዝብ ኤጀንሲው የግል ግምገማ ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ፣ ለወላጆቹ ስለሚከተሉት ነጥቦች መረጃ ይሰጣል፡

- በግል የሚሰጥ የትምህርት ግምገማ የት ሊገኝ እንደሚችል፤ እንዲሁም
- ስለ ግል የትምህርት ግምገማ የሕዝብ ኤጀንሲው ያለውን መመዘኛዎች።

# የሕዝብ ኤጀንሲ መመዘኛዎች፡

አንድ የግል የትምህርት ግምገማ በሕዝብ ወጪ የሚደረግ ከሆነ፣ የግል የትምህርት ግምገማውን ለማግኘት የሚጠቀምባቸ መመዘኛዎች፣ ግምገማው የሚሰጥበት ቦታና የፈታኙን ብቃት ጨምሮ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ራሱ ግምገማን ሲያነሳሳ ከሚጠቀምባቸው መመዘኛዎች ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት፣ እነዚህ መመዘኛዎች ወላጁ የግል የትምህርት ግምገማ ከማግኘት መብቱ ጋር አብረው መሄድ አለባቸው። ከዚህ በላይ ከተገለጹት መመዘኛዎች በስተቀር በሕዝብ ወጪ የሚደረግ የግል የትምህርት ግምገማ ከማግኘት ጋር በተያያዘ የሕዝብ ኤጀንሲው የቅድመ-ሁኔታዎችና የጊዜ ገደቦች ጫና መፍጠር አይችልም።

# በሕዝብ ወጪ ከሚደረግ ግምገማ ጋር በተያያዘ የወላጅ መብት፡

ወላጆች የሕዝብ ኤጀንሲ በሰጠው ግምገማ የማይስማሙ ከሆነ በሕዝብ ወጪ የሚደረግ የግል ትምህርታዊ ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው።[4] ወላጆች የግል ትምህርታዊ ግምገማ በሕዝብ ወጪ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ካቀረቡ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው አላስፈላጊ መዘግየት ሳያደርግ ጥያቄውን በማጽደቅ ግምገማውን በሕዝብ ወጪ ለማመቻቸት ስላሉት ሂደቶች ለወላጅ ምክር መስጠት ወይም ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

የሕዝብ ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት አስጀምሮ ውሳኔው የሕዝብ ኤጀንሲው ግምገማ ተገቢ ነው የሚል ከሆነ፣ ወላጆች በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ የማግኘት መብታቸው አሁንም የተጠበቀ ቢሆንም በሕዝብ ወጪ ግን ሊሆን አይችልም።

ወላጆች የግል ትምህርታዊ ግምገማ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ካቀረቡ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው የሕዝብ ግምገማውን ወላጆች የተቃወሙበትን ምክንያት ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የወላጅ ማስረጃ አስፈላጊ አይደለም፣

የሕዝብ ኤጀንሲውም በሕዝብ ወጪ የሚደረገውን የግል ትምህርታዊ ግምገማ ለማቅረብ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲውን ግምገማ በችሎት ፊት ቀርቦ ለማስረዳት የፍትህ ሂደት ችሎት ለማስጀመር አላስፈላጊ መዘግየት መፍጠር የለበትም።

# በወላጅ አነሳሽነት የሚደረግ ግምገማ፡

ወላጆች ምንጊዜም ቢሆን የግል ትምህርታዊ ግምገማን፣ እራሳቸው በግላቸው ከሚመርጡት የሰለጠነ ባለሙያ በራሳቸው ወጪ የማግኘት መብት አላቸው። ቡድኑም፣ ለልጁ መቅረብ በሚገባው FAPE ላይ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ወቅት፣ በወላጆች አነሳሽነት፣ በወላጆች የግል ወጪ፣ ከተደረገው ግምገማ የተገኘውን መረጃ፣ ግምገማው የሕዝብ ኤጀንሲውን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፣ ማጤን ይኖርበታል።[5] እንደዚሁም ደግሞ፣ በወላጆች የግል አነሳሽነት የተደረገው የግል የግምገማ ውጤት የተጠቃሹን ልጅ ጉዳይ በሚመለከት የፍትህ ሂደት ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል።

[4] 34 CFR § 300.502(b)(5).

[5] 34 CFR § 303.502(c).

# ግምገማ እንዲደረግ በአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) የሚቀርብ ጥያቄ፡

አንድ የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) ከአስተዳደር ችሎት ቢሮ (OAH) ጋር አብሮ በመሆን አንድ ይግል ትምህርታዊ ግምገማ በችሎት ላይ የሚሰማ ጉዳይ አካል ሆኖ እንዲቀርብ ከጠየቀ፣ ግምገማው የሚካሄደው በሕዝብ ወጪ መሆን ይኖርበታል።

# ምትክ ወላጆች

**IEP እና IFSP**

**34 C.F.R. § 300.519 እና § 303.422**

የአካባቢው መሪ ኤጀንሲ፣ የአካባቢው የትምህርት ስርዓት፣ አሊያም ደግሞ በአንዳንድ አጋጣሚዎች አንድ ዳኛ በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቁ ለሆነ ልጅ ምትክ ወላጅ ሊመድብ ይችላል፡

- ወላጁ መታወቅ ካልቻለ፤
- ምክንያታዊ ከሆነ ጥረት በኋላ የሕዝብ ትምህርት ቤቱ የልጁን ወላጅ ማግኘት ካልቻለ፤ ወይም
- ልጁ በሜሪላንድ ስቴት ጥበቃ ስር ያለ ከሆነ፡፡
- የሕዝብ ኤጀንሲው ልጁ ምትክ ወላጅ እንደሚያስፈልገው ከወሰነ ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምትክ ወላጅ መመደቡን ለማረጋገጥ መሪ ኤጀንሲው አሳማኝ ጥረቶችን ማድረግ አለበት።

# ምትክ ወላጅ ለመሆን ያሉ መስፈርቶች፡

- ከልጁ ጋር የጥቅም ግጭት የሌለበት
- ልጁን ለመወከል የሚያስችል በቂ ዕውቀት እና ክህሎት መኖር፤
- የስቴቱ ወይም የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ለልጁ ወይም ለልጁ ቤተሰቦች በማቅረብ ላይ የተሰማራ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኛ ያልሆነ፤

እንደ ምትክ ወላጅ አንዴ ከተሾመ በኋላ ምትክ ወላጁ ለሁሉም ዓላማዎች ከወላጅ ጋር ተመሳሳይ መብቶች አሉት።

- ምትክ ወላጅ ለመሆን በሕዝብ ኤጀንሲ ስለተከፈለው ብቻ ምትክ ወላጁ የኤጀንሲ ሰራተኛ ነው ተብሎ አይወሰድም፡፡

የአካባቢው መሪ ኤጀንሲ ወይም የአካባቢ ትምህርት ዘዴ ስለ ምትክ ወላጅ ምደባ የግዛቱን የትምህርት ቤቶች ሃላፊ ወይም ተወካዩን ማሳወቅ አለበት፡፡ ምትክ ወላጅ ከሚከተሉት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ ልጁን መወከል አለበት፡

- ልጅን መገምገም እና መከታተል፤
- የልጁን IFSP አገልግሎት ዕድገት መከታተል፣ አመታዊ እና ጊዜያዊ ግምገማዎችን ይጨምራል፤
- የልጁን IEP ማዘጋጀት፣ መከለስ እና ማሻሻል፤
- ለልጁ እና ለወላጆቹ በ IFSP አገልግሎት በኩል የልጅነት ጊዜ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን ቀጣይ አቅርቦት፤ ወይም
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን በ IEP በኩል ማቅረብ።

# የመረጃ ሚስጥራዊነት

**IEP እና IFSP**

**34 C.F.R. §§ 300.610-627 እና 34 C.F.R. §§ 303.401-417**

**ወላጆች የልጃቸውን ሬኮርዶች የማየትና ሬኮርዱ ስህተት አለው ብለው ካሰቡ የሕዝብ ኤጀንሲው ሬኮርዱን እንዲያስተካክል የመጠየቅ መብት አላቸው። የግላዊ መለያ መረጃዎችን ይፋ ከመደረጋቸው በፊት የወላጆች የስምምነት ፈቃድ መገኘት አለበት፣ ሆኖም ከዚህ በታች እንደተመለከተው ስምምነት መስጠት የማያስፈልግባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ወላጆች የልጃቸውን የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም ትምህርታዊ ሬኮርዶች የሕዝብ ኤጀንሲው በግልና በምስጢር ይይዝልኛል ብለው የመጠበቅና የልጃቸው ትምህርታዊ መረጃ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም ትምህርታዊ አገልግሎቶች ለማቅረብ የማያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ እንዲደመሰስላቸው የሕዝብ ኤጀንሲውን የመጠየቅ መብት አላቸው።**

# ትርጓሜዎች፡

ድምሰሳ ማለት፣ የአንድን ግለሰብ ማንነት ለመለየት ያስችሉ የነበሩ ማንኛቸውም ዓይነት ግለሰባዊ መለያዎች ከእንግዲህ ወዲያ ፈጽሞ ሊታውቁ እንዳይችሉ አድርጎ መደምሰስ ወይም ማጥፋት ማለት ነው።

የትምህርት ሬኮርዶች ማለት፣ "የትምህርት ሬኮርዶች" በሚለው 34 C.F.R. ክፍል 99 ትርጓሜ (የቤተሰብ የትምህርት መብትና የመረጃ ምስጢራዊነት [FERPA] የ 1974 ድንጋጌ) ሥር የተመለከቱ ሬኮርዶች ማለት ነው።

የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ መዛግብት ማለት በ IDEA ክፍል C እና በዚህ ክፍል ውስጥ ባሉት መመሪያዎች መሰረት መሰብሰብ፣ ተጠናቅረው መያዝ፣ ወይም ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው አንድ ልጅን የተመለከቱ ሁሉም መዝገቦች ማለት ነው።

ተሳታፊ ኤጀንሲ ማለት፣ በ IDEA ክፍል B ሥር በተመለከተው መሠረት፣ የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን የሚሰበስብ፣ አጠናቅሮ የሚይዝ፣ ወይም የሚጠቀም፣ ወይም እነዚህን መረጃዎች ለማግኘት የሚቻልበት ማንኛውም ኤጀንሲ ወይም ተቋም ማለት ነው። በክፍል C ስር አንድ ተሳታፊ ኤጀንሲ መሪ ኤጀንሲውን እና የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎት ሰጪዎችን እና ማንኛውንም የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ማንኛውም ግለሰብ ወይም አካልን ያካትታል። ለክፍል C አገልግሎቶች የገንዘብ ምንጭነት ብቻ የሚሰሩ የመጀመሪያ ደረጃ የሪፈራል ምንጮችን፣ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲዎችን (እንደ ስቴት Medicaid ወይም CHIP ፕሮግራም) ወይም የግል ተቋማትን (እንደ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ያሉ) አያካትትም።

ግለሰባዊ መለያ መረጃዎችም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

- የልጅ ስም፣ የወላጆች ስም፣ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ስም፣
- የልጁ መኖሪያ አድራሻ፣
- ግለሰባዊ መለያ፣ ለምሳሌ የልጁ ሶሻል ሴክዩሪቲ ቁጥር፣ ወይም
- የልጁን ማንነት በሚዛናዊ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችሉ የግለሰባዊ መግለጫዎች ዝርዝር ወይም ሌሎች መረጃዎች።

በ IFSP አገልግሎት ለሚያገኙ ልጆች የግለሰባዊ መለያ መረጃዎች የሚከተሉትንም ያጠቃልላሉ፡

- ቀጥተኛ ያልሆኑ መለያዎች፣ ለምሳሌ የልጁ የትውልድ ቀን፣ የትውልድ ቦታ እና የእናት የቅድመ ጋብቻ ስም ስም፤
- በተናጠል ወይም በጥምረት፣ ከተዛማጅ ሁኔታዎች ጋር ልጁን በተመጣጣኝ ሁኔታ ለይቶ እንዲያውቅ የሚያስችለው የግል ዕውቀት የሌለውን አንድ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ምክንያታዊ ሰው ከአንድ የተወሰነ ልጅ ጋር የተገናኙ ወይም የሚገናኙ ሌሎች መረጃዎች፣ ወይም
- ከትምህርት መዝገቡ የሚዛመደውን የተማሪ ማንነት እንደሚያውቅ የትምህርት ኤጀንሲው ወይም ተቋሙ በምክንያታዊነት በሚያምነው ሰው የተጠየቀ መረጃ።

# ከለላዎች፡

እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ፣ የግላዊ መለያ መረጃዎችን ሲሰበስብ፣ አጠናቅሮ ሲያስቀምጥ፣ ለሌሎችም ሲያስተላልፍ፣ መረጃዎቹንም ሲደመስስ/ሲያጠፋቸው፣ ምስጢራዊነታቸውን በጥንቃቄ ይጠብቃል። የግላዊ መለያ መረጃዎችን በጥንቃቄ ለመጠበቅ እንዲያስችለውም፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ከኤጀንሲው አንዱን ባለሥልጣን በዚህ ሥራ በኃላፊነት ላይ ይመድባል። ከነዚህ የመከላከያ ሥርዓቶች መሰናዶዎች በተጨማሪም፣ የፌዴራላዊና ክፍለ ግዛታዊ ሕጎችና ደንቦችም እንደዚሁ የትምህርት ሬኮርዶችን ደህንነት መጠበቅን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋሉ። ግላዊ መለያ መረጃዎችን የሚሰበስቡ፣ ወይም መረጃዎቹን የሚጠቀሙ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ሠራተኞች የሆኑ ሁሉ፣ እነዚህን የግል መለያ መረጃዎችን ጥብቅ ምስጢራዊነት ለመጠበቅ የስቴት ፖሊሲዎችንና አፈጻጸማዊ ሂደታቸውን አስመልክቶ ተገቢውን ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ፣ ለሕዝብ ቁጥጥር በሚያመች መልኩ፣ ለግለሰባዊ መለያነት ከሚያገለግሉ መረጃዎች ጋር ግንኙነት የሚኖራቸውን ሠራተኞቻቸውን ስምና የሥራ ኃላፊነት ዝርዝር በግልጽ መዝግበው ያስቀምጣሉ።

# ስምምነት፡

መረጃው በትምህርት መዛግብት ውስጥ የተካተተ እና በ 34 C.F.R. ክፍል 99 መሰረት ያለ ወላጅ ፈቃድ ይፋ ማድረግ

የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ከተሳታፊ ኤጀንሲዎች ባለሥልጣናት ውጪ ለሆኑ ወገኖች የክፍል B መስፈርቶችን ለሚሟላት አላማዎች ተለይተው የሚታወቁ መረጃዎች ይፋ ከመደረጋቸው በፊት የወላጅ ስምምነት መገኘት አለበት። በ IDEA (IEP) ክፍል B ስር የሽግግር አገልግሎቶችን ለሚሰጡ ወይም ለሚከፍሉ ለተሳታፊ ድርጅቶች ባለሥልጣናት በግል የሚለይ መረጃ ከመልቀቁ በፊት፣ የህዝብ ኤጀንሲው የወላጆችን ፈቃድ ወይም በስቴቱ ሕግ መሠረት ለአካለ መጠን የደረሰ ብቁ የሆነ ልጅ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤ እንዲሁም አንድ ልጅ በወላጅ መኖሪያ ት/ቤት ዲስትሪክት ውስጥ በማይገኝ የግል ትምህርት ቤት ከተመዘገበ ወይም ሊመዘገብ ከሆነ፣ የግል ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ባለሥልጣናት እና በወላጅ መኖሪያ LEA ባለሥልጣናት መካከል ማንኛውም የልጁ ግላዊ መለያ መረጃ ከመለቀቁ በፊት የወላጅ ፈቃድ ማግኘት አለበት።(6)

ስቴቱ ያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሥርዓታዊ መመሪያዎች፣ ምስጢራዊነትን መጠበቅን ጨምሮ፣ በ IDEAና FERPA መሠረት መከበራቸውን ለማረጋገጥ፣ የሚጠቀምባቸውን ቅጣቶች ጨምሮ፣ MSDE ለሕዝብ ድርጅቶች ሥርዓታዊ መመሪያዎችን ነድፎ አዘጋጅቷል። አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ የመንግሥት ኤጀንሲ በ IDEA መሠረት ሚስጥራዊነትን መጣሱን ካመነ ጉዳዩን ለመፍታት የስቴት አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል።

እያንዳንዱ የሕዝብ ኤጀንሲ፣ የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን ምስጢራዊ አጠባበቅ በተመለከተ ወላጆች የተሟላ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ማስታወቂያዎቹ ለወላጆች የቱን ያክል በበቂ ሁኔታ መዳረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉት ዝግጁ ሥርዓታዊ መመሪያዎች ሊኖሩት ይገባል። ይህም ከዚህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡

- ማስታወቂያው በክፍለ ግዛቱ ውስጥ ለሚኖሩት የተለያዩ ማህበረሰቦች በትውልድ ቋንቋቸው ተዘጋጅቶ የቱን ያክል እንደተሰራጨ የሚያሳይ መግለጫ፣
- የግል መለያዎቻቸው ተመዝግቦ የተያዘላቸው ልጆችና የተጠየቁ ተጨማሪ መረጃዎች፣
- ተሳታፊ ድርጅቶች የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን በአግባቡ ማስቀመጥን፣ ለሌላ ሶስተኛ ወገን መስጠትን፣ ጠብቆ ማቆየትንና መደምሰስን በተመለከተ ሊከተሏቸው የሚገቡ ፖሊሲዎችና ሥርዓታዊ መመሪያዎችን የሚያመለክት አጭር የማጠቃለያ መግለጫ፣
- ወላጅ ስምምነቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ባልሆነበት አጋጣሚ ኤጀንሲው የተጠቀመባቸውን ፖሊሲዎችና ሥርዓታዊ መመሪያዎች የሚያሳይ መግለጫ፣ እና
- በ FERPA ስራ ያሉትን እና ለማስፈጸም በሚለው በ 34 C.F.R. ክፍል 99 ሥር የተመለከቱትን ደንቦች ጨምሮ፣ ይህን መረጃ በተመለከተ ወላጆችና ልጆች የሚኖራቸውን መብቶች የሚገልጽ።

ከማንኛውም ዓይነተኛ መለያ፣ ከቦታና ከግምገማ እንቅስቃሴ ቀደም ብሎ ማስታወቂያው መታተም፣ ወይም በጋዜጦች፣ ወይም በሌሎች የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ሁሉ በበቂ ስርጭት ለሕዝብ እንዲዳረስ ሆኖ መታወጅ ይኖርበታል።

በተጨማሪም፣ የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን የሚሰበስቡና የሚጠቀሙ የተሳታፊ ድርጅቶች ኦፊሴላዊ (የታወቁ) ሠራተኞች ውጪ፣ ወይም በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት የአንድን የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪ የ FAPE ፍላጎቶችን ማጤንና የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ማሟላትን ከሚመለከት ውጪ በሆነ መልኩ፣ የግላዊ መለያ መረጃዎችን ይፋ ሊደረጉ አይችሉም። ከቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወደ ቅድመ-ትምህርት ቤት አገልግሎቶች በሚሸጋገርበት ጊዜ መሪው ኤጀንሲ ለ MSFE እና ለአከባቢው ትምህርት ቤት ስርዓት በ 34 C.F.R. § 303.209(b)(1)(i) በሚፈለገው መሰረት ልጁ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሊሆን እንደሚችል ማሳወቂያ ይሰጣል። ይህ ማሳወቂያ በ 34 C.F.R. § 303.209(b)(1) እና § 303.401 በሚፈለገው መሰረት የልጁን ስም፣ የትውልድ ቀን እና የወላጅ ግንኙነት መረጃን ያጠቃልላል። አካል ጉዳተኛ የሆነ ልጅ ስለፈጸመው ሪፖርት ለሕግ አስከባሪ አካላት እና ለፍትሕ ባለሥልጣናት በሚደረገው መምሪያ እና እርምጃ ላይ ይፋ ማድረግ በ FERPA በተፈቀደው መጠን የወላጅ ፈቃድ አያስፈልገውም።

# የመጎብኘት/የመመልከት መብቶች፡

የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት እና ቤተሰቦች የአካባቢው መሪ ኤጀንሲ ያለምንም ወጪ ለወላጆች የልጆቻቸውን የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ መዝገብ የመጀመሪያ ቅጂ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የአካባቢው መሪ ኤጀንሲ በተጨማሪም ለወላጆች ያለምንም ወጪ፣ የእያንዳንዱን ግምገማ ቅጅ፣ የልጁን ምዘና፣ የቤተሰብ ምዘና እና IFSP ከእያንዳንዱ የ IFSP ስብሰባ በኋላ በተቻለ ፍጥነት መስጠት አለበት። እያንዳንዱ የሕዝብ ኤጀንሲ ወላጆች ልጃቸውን በሚመለከት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም ኤጀንሲው የልጁን ማንነት መለያ፣ ግምገማና የትምህርት ምደባ፣

(6) 34 CFR § 300.622.

እንደዚሁም የIFSP ዝግጅትና ሥራ ላይ ማዋል እና የልጁን የ FAPE አቅርቦት አስመልክቶ የሚጠቀምባቸውን መረጃዎች ሁሉ አይተው እንዲመረምሩና ካስፈለገም እንዲያስተካክሉ/እንዲከልሱ ይፈቅዳል። በIFSP በኩል የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት እና ቤተሰቦች የአካባቢው መሪ ኤጀንሲ ያለምንም አላስፈላጊ መዘግየት IFSPን የተመለከተ ስብሰባ፣ ወይም ከማንኛውም የፍትህ ችሎት ሂደት ስብሰባ በፊት ጥያቄዎች በቀረቡለት በ 10 ቀናት ውስጥ ማድረስ አለበት፡፡

በ IEP በኩል አገልግሎት ለሚያገኙ ሕጻናት፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ካለምንም አላስፈላጊ የጊዜ ማጓተት፣ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ሁሉ IEPን በተመለከተ ከሚደረግ ስብሰባ በፊት፣ ወይም ማንኛውም የመፍትሄ ወይም የፍትህ ሂደትን የሚመለከት ሸንጎ ከመሰየሙ በፊት፣ እንደዚሁም ጥያቄው ከቀረበ ከ 45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠትን ማክበር ይኖርበታል። በዚህ ክፍል ሥር የሚጠቀሱ የትምህርት ሬኮርዶችን የመመርመርና የመከለስ የወላጅ መብቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ሬኮርዶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ሚዛናዊ የማብራሪያና የትርጓሜ ጥያቄዎች ከተሳታፊ ኤጀንሲው የሚሰጥ ምላሽ፣
- የሬኮርድ ቅጂዎችን ለወላጆች አለመስጠት ወላጆች ሬኮርዶችን አይተው ለመመርመርና ለመከለስ እንዳይችሉ መሠረታዊ መብቶቻቸውን አጥብቆ የሚጋፋ በመሆኑ፣ ኤጀንሲው የሬኮርድ ቅጂዎች ለወላጆች እንዲሰጥ ለመጠየቅ፣ እና
- ወላጆች ሬኮርዶችን የሚመረምርና የሚከልስ ተወካይ እንዲኖራቸው ለማድረግ።

የሕዝብ ኤጀንሲው እንደ አሳዳጊነት፣ መለያየት እና ከትዳር መፋታት የመሳሰሉትን ጉዳዮች አስተናጋጅ (ገዢ) በሆነው የስቴቱ ተፈፃሚ ሕግ ሥር በተመለከተው መሠረት፣ ወላጆች በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንደሌላቸው ካልተነገረው በስተቀር፣ ኤጀንሲው ወላጆች ከልጃቸው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሬኮርዶች ለመመርመርና ለመከለስ ስልጣኑ እንዳላቸው አድርጎ ሊገምት ይችላል።

# የመጎብኘት/የመመልከት ሪኮርድ፡

እያንዳንዱ የሕዝብ ኤጀንሲ፣ ከወላጆችና አግባብነት ካላቸው ወይም ስልጣኑ ካላቸው የሕዝብ ኤጀንሲ ሠራተኞች ውጪ፣ በ IDEA ክፍል C ወይም ክፍል B ሥር በተመለከተው መሠረት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት ሬኮርዶችን ለማየት/ለመጎብኘት ዕድል ያገኙ ግለሰቦችን ስም፣ ግለሰቡ የጉብኝቱን ዕድል ያገኙበትን ቀንና ጉብኝቱ እንዲፈቀድለት ያስቻለውን ምክንያት/ዓላማ፣ በማካተት መዝገቦ ይይዛል። አንድ የትምህርት ሬኮርድ፣ ከአንድ በላይ ልጆችን ሬኮርድ አካትቶ የሚይዝ ከሆነ፣ ወላጆች ልጃቸውን የሚመለከተውን ሬኮርድ ብቻ ለይተው በማውጣት ነው የማየት፣ የመመርመርና የመከለስ መብት የሚኖራቸው፣ አለበለዚያም እነሱን የሚመለከተውን/የሚፈልጉት ሬኮርድ የትኛው እንደሆነ ተለይቶ ይነገራቸዋል። እያንዳንዱ የሕዝብ ኤጀንሲ በኤጀንሲው የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት ሬኮርዶችን ዓይነትና፣ የሬኮርዶቹ ክምችትም የሚገኝበትን ቦታ፣ ወላጆች ሲጠይቁ ይሰጣል። ወላጆች ሬኮርዶቹን ለመመርመርና ለመከለስ ያላቸውን መብት ከመጠቀም የሚያግዳቸው እስካልሆነ ድረስ፣ እያንዳንዱ የሕዝብ ኤጀንሲ ለወላጆች ለሚደረጉ የትምህርት ሬኮርዶች ቅጂዎች ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል። አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ከትምህርት ሬኮርዶች ውስጥ መረጃ ለመፈለግ ወይም ለማውጣት ክፍያ መጠየቅ አይችልም።

# በወላጅ ጥያቄ መሠረት ሬኮርዶችን ማስተካከል፡

በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት ሬኮርዶች ውስጥ ያለው መረጃ ትክክል አይደለም፣ ወይም አሳሳች ነው ወይም ምስጢራዊነትን ወይም ሌሎች የልጁን መብቶች ይጋፋል ብለው ባመኑ ጊዜ፣ ወላጆች መረጃው ይስተካከል ዘንድ መረጃውን የያዘውን የሕዝብ ኤጀንሲ ሊጠይቁ ይችላሉ። የሕዝብ ኤጀንሲውም ጥያቄውን ከቀበለበት ዕለት አንስቶ፣ በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ፣ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት መረጃውን ያስተካክል እንደሆነ ይወስናል። የሕዝብ ኤጀንሲው በቀረበለት ጥያቄ መሠረት መረጃውን የማስተካከሉን ጥያቄ እንደማይቀበለው ከወሰነ፣ ይህንኑ እምቢታውን ለወላጆች ማሳወቅና፣ ወላጆችም የትምህርት ሬኮርዶችን በተመለከተ ያነሱትን ጥያቄ ችሎት ፊት አቅርበው የመሞገት መብት እንዳላቸው ኤጀንሲው ሊያሳውቃቸው ይገባል። የትምህርት ሬኮርዶች መረጃ ሙግትን የሚሰማው የፍትህ ሂደት ሸንጎ የሚከናወነው በ 34 C.F.R. §99.22 ውስጥ በተመለከተው በ FERPA መሠረት መሆን አለበት።

የሕዝብ ኤጀንሲው፣ በተጠየቀ ጊዜ፣ በትምህርት ሬኮርዶች ውስጥ የሚገኝ መረጃን በተመለከተ የተነሳው ሙግት ለችሎት

ቀርቦ፣ እንደተባለው መረጃው ትክክለኛነት የጎደለው አለመሆኑን፣ አሳሳች አለመሆኑን፣ ወይም ምስጢራዊነትን ወይም ሌሎች የልጁን መብቶች የሚጻረር አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይቻለው ዘንድ ለችሎት እንዲቀርብ ዕድል ይሰጣል። ከችሎቱ በተገኘው ውጤት መሠረት የሕዝብ ኤጀንሲው የተባለው መረጃ ትክክለኛነት የጎደለው፣ ወይም አሳሳች፣ ወይም ምስጢራዊነትንም ሆነ ወይም ሌሎች የልጁን መብቶች የሚጋፋ ሆኖ እንዳገኘው ከወሰነ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት መረጃውን ያስተካክላል፣ አፈጻጸሙንም በጽሑፍ ለወላጆች ያሳውቃል። ከችሎቱ በተገኘው ውጤት መሠረት የሕዝብ ኤጀንሲው የተባለው መረጃ ትክክለኛነት የጎደለው አይደለም፣ አሳሳችም አይደለም፣ ወይም ምስጢራዊነትንም ሆነ ሌሎች የልጁን መብቶች የሚጥስም አይደለም ብሎ ከወሰነ፣ ወላጆች በተባለው መረጃ ላይ ያላቸውን አስተያየት በማከል፣ ስለልጁ የያዙትን ተጨማሪ መረጃ የማቅረብ መብት እንዳላቸው ኤጀንሲው ሊያሳውቃቸው ይገባል።

በልጅዎ ሬኮርዶች ላይ የሚታከለው ማንኛውም ማብራሪያም፡

- ሬኮርዱ፣ ወይም ክርክር የተነሳበት የሬኮርዱ ክፍል የሕዝብ ኤጀንሲው እጅ እስካለ ድረስ፣ የሬኮርዶቹ አካል ሆኖ በሕዝብ ኤጀንሲው እጅ መቆየት አለበት፣ እንዲሁም
- የልጁ ሬኮርድ፣ ወይም ክርክር የተነሳበት የሬኮርዱ ክፍል፣ በሕዝብ ኤጀንሲው አማካኝነት ለማንኛውም ሌላ ወገን ከተሰጠ፣ ማብራሪያውም ጭምር አብሮ መገለጥ አለበት።

# መረጃን የመደምሰስ አሰራር ሂደቶች፡

የሕዝብ ኤጀንሲው በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ

የዋሉ በግል ሊያሳውቁ የሚችሉ መረጃዎች ከእንግዲህ ወዲያ ለልጁ ለሚሰጡ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም ትምህርታዊ አገልግሎቶች አስፈላጊ አይደሉም ብሎ ባመነ ጊዜ፣ ይህንኑ ለወላጆች ማሳወቅ ይጠበቅበታል። መረጃውም፣ ወላጆች ሲጠይቁ መደምሰስ ይኖርበታል። ሆኖም በክፍል B ስር የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን ለሚቀበሉ ተማሪዎች፣ የተማሪው ስም፣ የስልክ ቁጥሩ፣ የትምህርት ውጤቱ፣ የተሳትፎ ሬኮርዱ፣ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ትምህርቱን የተከታተለባቸው ቀናት፣ ያጠናቀቀው የክፍል ደረጃ፣ እና ስንተኛ ዓመትን እንዳጠናቀቀ የሚያሳየው የተማሪው ቋሚ ሬኮርድ ያለምንም ጊዜ ገደብ በኤጀንሲው ተይዞ ሊቆይ ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ በክፍል C ስር የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን ለሚቀበሉ ልጆች፣ የልጁ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ የወላጅ መገኛ መረጃ (አድራሻ እና የስልክ ቁጥርን ጨምሮ)፣ የአገልግሎት አስተባባሪ (ዎች) ስም እና የ EIS አገልግሎት አቅራቢ(ዎች) እና የመልቀቂያ መረጃዎች (የወጡበትን ዓመት እና ዕድሜ፣ እና ሲወጡ የገቡባቸው ማናቸውንም ፕሮግራሞች ጨምሮ) ያለ የጊዜ ገደብ ተይዘው ሊቆዩ ይችላሉ።

# የልጆች መብቶች፡

በ FERPA ሥር በተመለተው ደንብ መሠረት፣ የልጁ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት፣ በስቴቱ ሕግ መሠረት ብቁ የሚያደርገው ካልሆነ በስተቀር፣ ልጁ 18 ዓመት ሲሞላው፣ ወላጆች በልጃቸው ላይ የነበሯቸው መብቶች ሁሉ ወደ ልጁ ይተላለፋሉ። በ IDEA ክፍል B በተመለከተው መሠረት የወላጅ መብቶች ለአካለ መጠን ወደደረሰው ልጅ የሚተላለፉ ከሆነ፣ የ IDEA የመረጃ ምስጢራዊነት መስፈርቶችም ወደ ልጁ መዛወር አለባቸው። ሆኖም የሕዝብ ኤጀንሲው በ IDEA ሥር የሚጠበቅበትን ማስታወቂያ ለወላጅና ለልጁ መስጠት አለበት። በይበልጥ የተብራራ መረጃ ለማግኘት እባክዎን "የወላጅነት መብቶችን አካለ-መጠን ለደረሱ ልጆች ማስተላለፍ" የሚለውን ይመልከቱ።

# የዲሲፕሊን እርምጃን የተመለከቱ መረጃዎች፡

አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ፣ በአንድ ተማሪ ላይ የተወሰደ፣ ወይም ቀደም ሲል ተወስዶ የነበረ የሥነ-ምግባር እርምጃን የሚያሳይ መግለጫ፣ ልክ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ለሌለባቸው ተማሪዎች በሚደረገው ተመሳሳይ የሬኮርድ መያዝና የማስተላለፍ ሁኔታ፣ በልጁ ሬኮርድ ውስጥ አካትቶ ሊይዝ ይችላል፣ መግለጫውንም ያስተላልፋል። የሥነ-ምግባር እርምጃው እንዲወሰድበት የተደረገው ልጅ ባህርያት መግለጫን የተወሰዱ የሥነ-ምግባራዊ እርምጃዎችን፣ እና ማንኛውንም ለልጁ ሁለንተናዊ ደህንነት አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚገመቱ መረጃዎችና በልጁ ጉዳይ የገቡ/የተሳተፉ ሌሎች ግለሰቦችን ሊያካትት ይችላል። ልጁ ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ሲተላለፍ፣ የሬኮርድ ዝውውሩ የልጁን ወቅታዊ IEP እና ማንኛውም ቀደም ብሎ ወይም በወቅቱ በልጁ ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች ካሉ ማጠቃለል ይኖርበታል።

# የአእምሮና የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ዲሲፕሊን

**IEP**

## 34 C.F.R. §§ 300.530 -300.536

ከዚህ በታች ያለው መረጃ የሚመለከተው የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው፣ ዕድሜያቸው ከ 3 እስከ 21 ዓመት የሆነ፣ በተራዘመ IFSP ወይም IEP በኩል አገልግሎቶች የሚያገኙ ልጆችን ነው።

**የሕዝብ ኤጀንሲው የተወሰኑ የሥነ-ምግባር እርምጃ ልጃቸው ላይ ከወሰደ ወላጆች ትክክለኛ የሥርዓቶችና የመከላከያ ደንቦች የማግኘት መብት አላቸው። በትምህርት ዘመን ውስጥ፣ አንድ ልጅ የስነ ሥርዓት ደንብ/ቦች በመተላለፍ ምክንያት ከ 10 ቀናት በላይ እንዲታገድ ከተደረገ፣ ከ 34 C.F.R. § 300.530(d) ጋር በሚጣጣም መልኩ ተማሪው ከወጣ በኋላ የሕዝብ ኤጀንሲው ለተማሪው ትምህርታዊ አገልግሎቶች መስጠት አለበት።**

# ትርጓሜዎች፡

ለዚህ ክፍል አገልግሎት የሚከተሉት ፍቺዎች ይተገበራሉ፡

- የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ነገር ማለት ማንኛውም መድሃኒት/ዕጽ፣ ወይም በ(21 U.S.C. 812(c)) በተመለከተው የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ-ነገሮች ድንጋጌ ውስጥ በተመለከተው የአፈጻጸም መርሀ-ግብር I፣ II፣ III፣ IV ወይም V በክፍል 202(c) ሥር የተጠቀሰ ክልክል/ሕገ-ወጥ ነገር።
- ሕገ-ወጥ እፅ (ድረግ) ማለት የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ነገር ማለት ሲሆን፣ በሕጋዊ መንገድ ተይዞ የተገኘ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋለ፣ ሕጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ቁጥጥር ሥር ወይም ሌላ በ IDEA መሠረት ስልጣን ባለው ሰው አማካኝነት ተይዞ የተገኘን፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋለን፣ ወይም ሌላ በፌዴራላዊ ሕግ ፈቃድ ሥር ያሉትን አያጠቃልልም።
- መሣሪያ የሚለው ቃል በዩናይትድ ስቴትስ ሕግ ክፍል 930 በመጀመሪያ ንኡስ ክፍል (g) ርዕስ 18፣ በጽሑፍ አንቀጽ/ፓራግራፍ (2) ሥር እንደተመለከተው "አደገኛ መሣሪያ" የሚለውን የቃል ትርጉም ይይዛል።
- ከባድ የሰውነት ጉዳት የሚለው ቃል በዩናይትድ ስቴትስ ሕግ ክፍል 1365 በመጀመሪያ ንኡስ ክፍል (g) ርዕስ 18፣ በጽሑፍ አንቀጽ/ፓራግራፍ (3) ሥር እንደተመለከተው "ከባድ የሰውነት ጉዳት" የሚለውን የቃል ትርጉም ይይዛል።

# የትምህርት ቤት ባልደረቦች ሥልጣን፡

የትምህርት ቤቱ ባልደረቦች፣ የትምህርት ቤቱን የሥነ-ሥርዓት ደንብ ለጣሰው የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪ የትምህርት ምደባ ለውጥ ማድረግ የሚያስፈልግ እንደሆነ ለማየት ጉዳዩን በዝርዝር እየተመለከቱ የተለዩ ሁኔታዎች ካሉም ያጤናሉ።[7]

የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች የአካል ጉዳተኛ የሆነውን ልጅ አሁን ካለው ምደባ ወደ ተገቢ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቅንብር፣ ሌላ ዝግጅት ማዛወር፣ ወይም እገዳ፣ በአንድ ጊዜ ከ 10 የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የትምህርት ቤቱን የሥነ ምግባር ደንብ በመጣስ ምክንያት፣ የአካል ጉዳት በሌለባቸው ልጆች ላይ በሚወስዱት እርምጃ መጠን እርምጃ ሊወስዱ የሚችሉ ሲሆን፣ ለተለዩ የስነምግባር ችግሮች በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት ውስጥ ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ለማይበልጥ ተጨማሪ እገዳዎች እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ (ይህም፣ እነዚህ እገዳዎች በ §300.536 መሠረት የምደባ ለውጥ የሚፈጥሩ እስካልሆነ ድረስ ነው)።[8]

የተማሪ የስነምግባር ደንብን የጣሰው ባህሪ የልጁ አካል ጉዳት የባህሪ መገለጫ ካልሆነ (ከዚህ በታች የባህሪ መገለጫዎች መወሰኛ ግምገማ ይመልከቱ) እና የዲሲፕሊን እርምጃው የምደባ ለውጥ በተከታታይ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ከሆነ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ለእንዲህ ዓይነቱ ልጅ የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ልጆች በተመሳሳይ ሁኔታ እና በተመሳሳይ ጊዜ የዲሲፕሊን አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፣ ይህም ከዚህ በታች በአገልግሎቶች አቅርቦት ውስጥ እንደተገለጸው

(7) 34 CFR § 300.530(a).

(8) 34 CFR § 300.536 (b)(1).

ትምህርት ቤቱ ለልጁ አገልግሎት መስጠት ከሚኖርበት ውጪ ላሉት ነው፡፡[9] እንደዚህ ላሉት አገልግሎቶች የልጁ የ IEP ቡድን ጊዜያዊ የትምህርት ሁኔታን ይወስናል።[10]

አካል ጉዳተኛ የሆነ አንድ ልጅ በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት ውስጥ ለ 10 የትምህርት ቀናት አሁን ካለው ምደባ ከታገደ በኋላ በሚቀጥሉት ቀናት በሚወገዱበት ጊዜ የመንግስት ኤጀንሲው ከዚህ በታች አገልግሎቶች አቅርቦት ውስጥ በተገለፀው መሠረት በሚፈለገው መጠን አገልግሎቶችን መስጠት አለበት።[11]

ለሁሉም ልጆች በሚፈለገው የዲሲፕሊን ፖሊሲ መሠረት በሕዝብ ቅድመ መዋለ ሕጻናት ፕሮግራሞች፣ በመዋዕለ ሕጻናት፣ በአንደኛ ክፍል ወይም በሁለተኛ ክፍል ያሉ በዲሲፕሊን ምክንያት ሊታገዱ የሚችሉት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከትምህርት ቤቱ የሥነ-ልቦና ባለሙያ ወይም ከሌላ የአእምሮ ጤና ባለሙያ ጋር በመመካከር በጣልቃ ገብ እርምጃዎች እና ድጋፎች ሊቀነስ ወይም ሊወገድ የማይችል በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የማይቀር ስጋት ያለ መሆኑን ከወሰነ ብቻ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ርዕሰ መምህሩ ወይም የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተማሪውን ወላጅ ወይም አሳዳጊ በፍጥነት ማነጋገር አለባቸው። በተጨማሪም፣ ልጁ በአንድ ክስተት ከአምስት የትምህርት ቀናት በላይ ሊታገድ አይችልም። በሕዝብ

ቅድመ-መዋለ ሕጻናት ፕሮግራሞች፣ መዋለ ሕፃናት፣ አንደኛ ክፍል ወይም ሁለተኛ ክፍል ውስጥ ያሉ ልጆች ከፌዴራል ሕግ (COMAR 13A.08.01.11) ጋር በሚስማማ ሁኔታ ብቻ ለአርባ አምስት የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ በላይ በዲሲፕሊን ሊወገዱ ይችላሉ።

# አገልግሎቶች፡

በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ለ 10 የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ በታች ለሆነ ጊዜ ከምደባው የተወገደ አካል ጉዳተኛ ልጅ አገልግሎት ማግኘት የሚችለው የህዝብ ኤጀንሲዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ለተወገደ የአካል ጉዳት የሌለበት ልጅ አገልግሎት ከሰጠ ብቻ ነው።

አንድ አካል ጉዳተኛ ልጅ ከልጁ ወቅታዊ ምደባ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ከተወገደ እና ባህሪው የልጁ የአካል ጉዳት መገለጫ ካልሆነ (*የባህሪ መገለጫዎች መወሰኛ ግምገማን ይመልከቱ*) ወይም የተወገደው በልዩ ሁኔታዎች ከሆነ (*ልዩ ሁኔታዎችን ይመልከቱ*)፡[12]

1. ምንም እንኳን በሌላ ሁኔታ ውስጥ ቢሆን (ይህ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ ሊሆን ይችላል)፣ እና በልጁ IEP ውስጥ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ለውጥ ለማምጣት በመደበኛ የትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ መሳተፉን እንዲቀጥል የትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘቱን (ያለውን FAPE ማግኘት) መቀጠል አለበት፤ እንዲሁም
2. ተማሪው፣ እንዳስፈላጊነቱ፣ የሥነ-ምግባር ጥሰቱ በድጋሚ እንዳይከሰት ለማረም እንዲረዱ ሆነው የተቀረጹ፣ ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማና የጠባይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብ አገልግሎቶችና ማሻሻያዎችን ማግኘት ይኖርበታል።

አካል ጉዳተኛ የሆነ ልጅ በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት ውስጥ ለ 10 የትምህርት ቀናት አሁን ካለው ምደባ ከታገደ በኋላ እና የአሁኑ መታገድ ለ 10 የትምህርት ቀናት በተከታታይ ወይም ከዚያ በታች የተከናወነ ከሆነ እና እገዳው የምደባ ለውጥ ካልሆነ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጓሜ ይመልከቱ)፣ ከዚያ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ቢያንስ ከአንድ የልጁ አስተማሪ ጋር በመመካከር ምንም እንኳን በሌላ ሁኔታ ውስጥ እና በልጁ የ IEP ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ለውጥ ለማምጣት፣ ልጁ በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ትምህርት ውስጥ መሳተፉን ለመቀጠል ምን ያህል አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ ይወስናሉ። እገዳው የምደባ ለውጥ ከሆነ (*በዲሲፕሊን እገዳ ምክንያት የሚደረግ የምደባ ለውጥን ይመልከቱ*)፣ ምንም እንኳን በሌላ ሁኔታ ውስጥ እና በልጁ የ IEP ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ለውጥ ለማምጣት፣ ልጁ በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ትምህርት ውስጥ መሳተፉን ለመቀጠል ምን ያህል አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ የልጁ የ IEP ቡድን ይወስናሉ።

# የባህሪ መገለጫዎች መወሰኛ ግምገማ

በሥነ ምግባር ጥሰት ምክንያት የተደረገን የምደባ ለውጥ ውሳኔን በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለመለወጥ፣

---

[9] 34 CFR § 300.530(c).

[10] Id.

[11] 34 CFR § 300.530(b)(2).

[12] 34 CFR § 300.530(d).

የሕዝብ ኤጀንሲው፣ ወላጅና አስፈላጊ የሆኑ የ IFSP ቡድን ወይም የ IEP ቡድን አባላት በጋራ በመሆን IFSPን ወይም IEPን፣ ማንኛውም የአስተማሪ ትዝብትንና ግምገማዎችን፣ እና ለውሳኔው አስፈላጊነት አላቸው ተብለው በወላጆች የቀረቡትን ማንኛቸውንም ዓይነት መረጃዎች ጨምሮ መርምሮ በጥያቄ ሥር ያለው ሥነ-ምግባር፡

- በልጁ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ምክንያት የመነጨ እንደሆነ ወይም ከአካለ ስንኩልናው ጋር ቀጥተኛና አሳማኝ ግንኙነት እንዳለው፣ ወይም
- በጥያቄ ሥር ያለው ሥነ-ምግባር የሕዝብ ኤጀንሲው የልጁ IFSP ወይም IEP በአግባቡ ካለመተርጎሙ በቀጥታ የመነጨ እንደሆነ።[13]

የ IEPው ቡድን ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ከሁለት አንዳቸው ተማሪውን የሚመለከቱ እንደሆነ ከወሰኑ፣ የተጠቀሰው የሥነ-ምግባር ችግር የተማሪው የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ነጸብራቅ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።[14] በተጨማሪም፣ የ IEP ቡድን የተመለከተው የልጁ ምግባር LEA የልጁን IEP ተግባራዊ ባለማድረጉ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን ከወሰነ LEA እነዚህን ጉድለቶች ለማስተካከል አፋጣኝ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡[15]

የሥነ-ምግባር ሁኔታው የልጁ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ነጸብራቅ ከነበረ የIFSPቡድኑ ወይም የ IEP ቡድኑ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡[16]

- ተግባራዊ የባሕርይ/የጸባይ ግምገማ ማካሄድና፣ ለተማሪው የሚረዳ የባሕርይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብ ዕቅድ አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ቀደም ብሎ ይህንኑ ያላደረገ ከሆነ፤
- የባሕርይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ባለበት ሁኔታ፣ ተማሪው ይሄው የባሕርይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብ ዕቅድ የነበረው ከሆነ፣ ባሕርዩን ለማረምና ለማስተካከል አስፈላጊ በሆነ መልኩ፣ ይህንኑ ነባር ዕቅድ እንደገና መገምገምና ማሻሻል፤[17] እንዲሁም
- ተማሪው በዕጽ/ድረግ፣ በመሳሪያ፣ ወይም በሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳትን በማድረስ ምክንያት ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የመማሪያ ቦታ እንዲዛወር በተደረገበት ሁኔታ ሳይሆን፣ ለጸባይ ማረሚያ ዕቅዱ ማሻሻያነት እንደሚረዳ በማሰብ ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲው ለልጁ አዲስ ምደባ ቢደረግ እንደሚሻል የተስማሙ ካልሆነ ተማሪው ወደተባረረበት ትምህርት ቤቱ እንዲመለስ ማድረግ አለበት።[18]

# ልዩ ሁኔታዎች፡

የትምህርት ቤት ባልደረቦች፣ የአንድ ተማሪ ሁኔታ ከታች ከተዘረዘሩት ነጥቦች ጋር ተገናዛቢነት ሲኖረው፣ የተከሰተው ሥነ-ምግባር ሁኔታው የልጁ አካል ጉዳት ነጸብራቅ ስለመሆን አለመሆኑ የተደረሰ ውሳኔ ኖረም አልኖረ፣ ተማሪውን እስከ 45 የትምህርት ቀናት ድረስ ወደ መሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ መላክ ይችላሉ፡

- ለስቴቱ ክፍለ ግዛት ወይም ለአካባቢው የሕዝብ ኤጀንሲ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ተማሪው፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ በትምህርት ላይ እንዳለ፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ የክብረ በዓል/ዝግጅት ቦታ ላይ መሳሪያ ይዞ ወይም ባለመሳሪያ ሆኖ ከተገኘ፤[19]
- ለስቴቱ ክፍለ ግዛት ወይም ለአካባቢው የሕዝብ ኤጀንሲ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ተማሪው፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ በትምህርት ላይ እንዳለ፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ የክብረ በዓል/ዝግጅት ቦታ ላይ የተከለከለ ዕጽ/ድረግ ይዞ ወይም ሲጠቀም፣ ወይም ሲሸጥ ወይም ለመሸጥ ሲያስማማ/ሲደልል ከተገኘ፤[20] ወይም
- ለስቴቱ ክፍለ ግዛት ወይም ለአካባቢው የሕዝብ ኤጀንሲ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ተማሪው፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ በትምህርት ላይ እንዳለ፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ የክብረ በዓል/ዝግጅት ቦታ ላይ በሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ

[13] 34 CFR § 300.530(e)(1)(i-ii).
[14] 34 CFR § 300.530(e)(2).
[15] 34 CFR § 300.530(e)(3).
[16] 34 CFR § 300.530(f)(1).
[17] 34 CFR § 300.530(f)(1)(ii).
[18] 34 CFR § 300.530(f)(2).
[19] 34 CFR § 300.530(g)(1).
[20] 34 CFR § 300.530(g)(2).

የአካል ጉዳት ካደረሰ።[21]

የ IEP ቡድን የቡድን ምደባ ለውጦች ለሆኑ እና እንዲሁም ተጨማሪ ስልጣን እና ልዩ ሁኔታዎች በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ላሉ እገዳዎች ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታን ይወስናል።

# የምደባ ለውጥ፡

የአካል ጉዳተኛ ልጅን ከልጁ ወቅታዊ የትምህርት ምደባ ለማገድ ዓላማዎች ከሆነ በሚከተለው ሁኔታ የምደባ ለውጥ ይከሰታል፡

- ማስወገዱ በትምህርት ዓመት ውስጥ ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ነው፤ ወይም
- መወገዱ በአጠቃላይ በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ስለሆነ ልጁ አንድ ቅጥን የሚያመለክቱ ተከታታይ እገዳዎች ተደርገዋል፤ ቀደም ባሉት ክስተቶች በተከታታይ የእገዳ ውጤት ያስከተሉ የልጁ ባህሪዎች ጋር የልጁ ባህሪ በእጅጉ ተመሳሳይ ነው፤ እና እንደ እያንዳንዱ የእገዳ ርዝመት ያሉ ተጨማሪ ምክንያቶች ስላሉት፣ ልጁ የታገደበት ጠቅላላ ጊዜ፣ እና እገዳዎቹ

  እርስ በእርስ ያላቸው ቅርበት።

የሕዝብ ኤጀንሲው የእገዳዎች ቅጥ የአመዳደብ ለውጥን ይመሰርት እንደሆነ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ ይወስናል። ይህ ውሳኔ በፍትህ ሂደት እና በፍርድ ሂደቶች በድጋሚ ቀርቦ ሊታይ ይችላል። ለትምህርት ምደባው ለውጥ ምክንያት ለሆነው መባረሩ፣ አንድ ተማሪ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ከትምህርቱ ታግዶ እንዲቆይ በሚደረግ ጊዜ፣ የሥነ-ምግባሩ ሁኔታ የአካለ ስንኩልነቱ ነጸብራቅ ሆነም አልሆነ፣ ወይም ተማሪው በዕጽ/ድረግ፣ በመሳሪያ፣ ወይም በሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት በማድረስ ምክንያት ወደ ጊዜያዊ የመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት ቦታ (IAES) እንዲዛወር በተደረገበት ሁኔታ፣ ተማሪው፣ ምንም እንኳን በሌላ ቦታ ሆኖ ቢሆንም፣ በአጠቃላዩ ሥርዓተ-ትምህርት መሳተፉን መቀጠል እንዲችልና፣ ለተማሪው በተዘጋጀው IEP ውስጥ የተካተቱትን ግቦቹን ለማሟላት የሚያደርገውን ጥረት ለመቀጠል የሚያስችሉትን አገልግሎቶች ማግኘቱን ይቀጥላል። በተጨማሪም ተማሪው፣ እንዳስፈላጊነቱ፣ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች በተደጋጋሚ እንዳይዘወተሩ ለማረም እንደሚረዱ ሆነው የተቀረጹ፣ ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማና የጠባይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችና ማሻሻያዎችን ማግኘት ይኖርበታል። የ IEP ቡድኑም ተስማሚዎቹን አገልግሎቶችና አገልግሎቶቹም የሚሰጡበትን ቦታ ይወስናል።

# የሥነ-ምግባር እርምጃ ይግባኝ/አቤቱታ፡

በልጃቸው የባሕርይ ነጸብራቅ ጉዳይ ላይ የተላለፈውን ውሳኔ፣ ወይም ከሥነ-ምግባር ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የተደረገውን ምደባ ወላጆች የሚቃወሙ ከሆነ የአቤቱታ ማመልከቻቸውን ለአስተዳደራዊ ሸንጎ ቢሮ (OAH) እና ለሕዝብ ኤጀንሲው በማቅረብ ጉዳዩ እንዲታይላቸው መጠየቅ ይችላሉ።[22] የሕዝብ ኤጀንሲው የልጁን ወቅታዊ ምደባ ይዞ ማቆየት ልጁ ላይ ወይም ሌሎች ላይ ጉዳት የማስከተሉ ዕድል ከፍተኛ ነው ብሎ ካመነ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ጉዳዩ እንዲታይለት የአቤቱታ ማመልከቻ ለ OAH እና ለወላጆች ሊያስገባ ይችላል። የመፍትሔ ስብሰባውን ለመተው ወይም የግልግል ሂደት ለመጠቀም ወላጆች እና LEA በጽሑፍ ካልተስማሙ በስተቀር በዚህ ክፍል ስር የፍትህ ሂደት ችሎት በሚጠየቅበት ጊዜ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስታወቂያ በደረሰ በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባ መደረግ አለበት፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ በ 15 የቀን መቁጠሪያ ቀን ጊዜ ውስጥ ለሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ በሆነ መልኩ ካልተፈታ በስተቀር የፍትህ ሂደት ችሎቱም ይቀጥላል።

የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) የፍትህ ሂደት ችሎት ያካሂዳል። ከላይ ከተሰጡት ማናቸውም ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ የፍትህ ሂደት ችሎት በሚጠየቅበት ጊዜ ሁሉ ችሎቱ የተፋጠነ እና ከ 34 CFR § 300.532(c) ጋር የሚስማማ መሆን አለበት፤ ችሎቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ 20 የትምህርት ቀናት ውስጥ መካሄድ አለበት፣ እና የችሎቱ መኮንኑ ከችሎቱ በኋላ ባሉት 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

---

(21) 34 CFR § 300.530(g)(3).

(22) 34 CFR § 300.532(a).

በሥነ-ምግባር እርምጃ ይግባኝ ላይ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ALJ፡

- ልጁ ቀደም ብሎ ወደተባረረበት ትምህርት ቤት እንዲመለስ ሊያደርግ ይችላል፣ ወይም
- ልጁ አሁን ባለበት ምደባው እንዳለ መቆየቱ በተማሪው በራሱ ላይም ሆነ በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተጨባጭ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል ብሎ ከወሰነ፣ ይህ ተማሪ ከ 45 ለማይበልጡ የትምህርት ቀናት ወደ ተስማሚ የመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ እንዲቀየር ተዕዛዝ ይሰጣል።
- በዚህ ክፍል መሠረት በተፋጠነ የፍትህ ሂደት ላይ የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ በ 34 CFR § 300.514 መሠረት ይግባኝ ማለት ይቻላል።[23]

ማስታወሻ፡ LEA ልጁን ወደ መጀመሪያው ምደባ መመለስ በልጁ ላይ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ካመነ ከላይ ያሉት ሂደቶች ሊደገሙ ይችላሉ።[24]

በወላጅ ወይም በሕዝብ ኤጀንሲ አቤቱታ በቀረበ ጊዜ፣ የALJውን ውሳኔ በመጠባበቅ፣ ወይም የተፈቀደው የጊዜ ገደብ (ከ 45 የትምህርት ቀናት የማይበልጥ) እስከሚያበቃ፣ ቀድሞ የሚሆነው እስከሚሆን ድረስ፣ ተማሪው በመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ ላይ ይቆያል፣ ወላጆቹ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር።

# ልጁ ገና ብቁ ሆኖ ካልተገኘ

ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ መሆናቸው ገና ሳይወሰን በፊት ማንኛውንም ደንብ ወይም ሥነ-ምግባር የጣሱ ተማሪዎችን በሚመለከት፣ ይህ የባሕርይ ግድፈት ከመከሰቱ በፊት፣ ተማሪው የአካል ጉዳት እንደነበረበት የሕዝብ ኤጀንሲው የሚያውቅ ከሆነ፣ የተፈቀደው መከላከያ ይገባናል ብለው ተማሪዎቹ ሊጠይቁ ይችላሉ።

የሕዝብ ኤጀንሲው ያውቃል የሚባለው፣ የሥነ-ምግባር እርምጃውን ለመውሰድ ምክንያት የሆነው የባሕርይ ግድፈት ከመከሰቱ በፊት፡

- የተባለው ተማሪ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት፣ ወላጆች ስጋታቸውን ለህዝብ ኤጀንሲው የቁጥጥር/ክትትል ወይም አስተዳደራዊ አባል፣ ወይም ለልጁ አስተማሪ፣ በጽሑፍ ገልጸው ከሆነ፣
- ወላጆቹ የግምገማ ጥያቄ አቅርበው እንደሆነ፣ ወይም
- የተማሪው አስተማሪ፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤቱ ባልደረባ፣ በልጁ ላይ የተስተዋሉ በግልጽ የሚታወቁ ተደጋጋሚ የሥነ-ምግባር/የባሕርይ ሁኔታዎችን አስመልክቶ፣ ያደረባቸውን ስጋት በቀጥታ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ሥራ መሪው፣ ወይም ለሌላ የሕዝብ ኤጀንሲ የቁጥጥር/ክትትል ባልደረባ ገልጸው ከሆነ።

የሕዝብ ኤጀንሲው አላወቀም የሚባለው፡

- ወላጆች የሕዝብ ኤጀንሲው ልጃቸውን እንዲገመግም ካልፈቀዱ፣
- ወላጆች የሕዝብ ኤጀንሲው ለልጃቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች እንዲሰጥ ካልፈቀዱ፣ ወይም
- ልጁ ተገምግሞ በ IDEA ፍቺ መሠረት የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ እንዳልሆነ ከተወሰነ።

የሕዝብ ኤጀንሲው፣ የሥነ-ምግባር እርምጃውን ከመውሰዱ ቀደም ብሎ ልጁ የአካል ጉዳት ሁኔታ የማያውቅ ከሆነ፣ ልጁ አንድ በተመሳሳይ የሥነ- ምግባር ጉድለት ላይ የተገኘ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት የሌለበት ተማሪ ከሚወሰድበት ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር እርምጃን የመቀበል ዕጣ ሥር ይወድቃል።

ለተማሪው ግምገማ እንዲደረግለት ጥያቄው በወላጅ የቀረበው፣ ተማሪው በወቅቱ በሥነ-ምግባር እርምጃ ሥር ባለበት ወቅት ከሆነ፣ ግምገማው በአፋጣኝ መደረግ ይኖርበታል። የውሳኔዎቹን ወጤቶች በመጠባበቅ ልይ ሳለም፣ ልጁ በትምህርት ቤቱ ባለሥልጣናት በተወሰነው የትምህርት ምደባ ላይ ይቆያል። በሕዝብ ኤጀንሲው ግምገማና በወላጆች በቀረበው መረጃ ላይ በመመሥረት፣ ልጁ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት አለበት ተብሎ ከተወሰነ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው የልዩ ፍላጎት ትምህርትና

[23] 34 CFR § 300.532(c)(5).
[24] 34 CFR § 300.532(b)(3).

ተዛማጅ አገልግሎቶችን ያቀርቡለታል፣ ከዚያም ሥነ-ምግባርን/ሥነ-ሥርዓትን የሚመለከቱ ሁሉም የሥርዓት ከለላዎች ይከተላሉ።

# ወደ ሕግ አስከባሪና የዳኝነት ባለሥልጣናት መተላለፍና የሚወሰድ እርምጃ

IDEA የሕዝብ ድርጅቶች አንድን ወንጀል፣ አግባብነት ላላቸው ባለሥልጣናትና ለሕግ አስከባሪ መዝገብ/ሪፖርት ከማድረግ አይከለክልም፡፡ የዳኝነት ባለሥልጣናትም በአንድ አካለ ስንኩል ልጅ ለተፈጸሙ ወንጀሎች የፌዴራላዊና ክፈለ ግዛታዊ ሕግጋትን በተግባር በማስፈጸም ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይችላሉ። ማንኛውም የወንጀል ዘገባን የሚያቀርብ ኤጀንሲ፣ በቤተሰብ የትምህርት መብትና የመረጃ ምስጢራዊነት ድንጋጌ (FERPA) እስከተፈቀደው ድረስ በመሄድ፣ የወላጅ ፈቃድ ተጨምሮበት፣ ወይም በፖሊሲው ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የወላጅ ፈቃድ የማይጠየቅባቸውንም በማካተት፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ሥነ-ምግባራዊ ሬኮርዶችን ቅጂዎች አግባብነት ላላቸው ባለሥልጣናት ያቀርባል።

# ወላጆች በተናጠል ልጃቸውን የግል ትምህርት ቤት

## ውስጥ በሕዝብ ወጪ ስለማስገባት

## IEP

## 34 CFR § 300.148

**IDEA፣ አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ አንድ ልጅ የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE)እንዲያገኝ አማራጭ ቢሰጠውም ወላጆቹ በፈቃደኝነት ልጃቸውን የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ማስገባት ከመረጡ የሕዝብ ኤጀንሲው፣ በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ያለን የአንድ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅን የትምህርት ወጪ፣ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ እንዲከፍል አያደርግም።**

አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ፣ ለተባለው ልጅ የሚመጥን FAPE ዝግጁ አድርጎ ባለበት ወቅት፣ ወላጆች ግን በራሳቸው ምርጫ ልጃቸውን በግል ትምህርት ቤት፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት ካለበት ቦታ ማስገባት ከፈለጉ፣ ለልጁ የሚጠየቀውን የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ወጪ፣ FAPE ዝግጁ አድርጎ የነበረው የሕዝብ ኤጀንሲ እንዲከፍል IDEA አያዝም። ሆኖም በፌዴራል ደንቦች መሠረት የሕዝብ ኤጀንሲው ልጁን ወላጆቻቸው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ከከተቷቸው ልጆች መሃል አንድኡ አድርጎ መመዝገብ አለበት።
የ FAPE ዝግጁነትና የገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ በወላጆችና በሕዝብ ኤጀንሲው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት፣ ከፍርድ ሸንጎ/ችሎት ፊት ቀርበው የዳኝነት ፍርዳቸውን ማግኘት ይኖርባቸዋል። ለበለጠ ዝርዝር መረጃ፣ "አለመግባባቶችን ስለመፍታት" የሚለውን ይመልከቱ።

ቀደም ሲል በአንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ሥልጣን ሥር፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ሲያገኙ የነበሩ የአንድ የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ወላጆች፣ ከሕዝብ ኤጀንሲው ፈቃድ ሳያገኙ፣ ወይም በሕዝብ ኤጀንሲው ባልተፈጸመ ዝውውር፣ ልጃቸውን በመዋለ-ሕጻናት ትምህርት ቤት፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲገባ ቢያደርጉና፣ ልጁ ወደ አዲሱ የሚማርበት ቦታ ከመዛወሩ በፊት የሕዝብ ኤጀንሲው ለልጁ የሚስማማ FAPE ዝግጁ ያላደረገ እንደነበረ በ ALJ ወይም በፍርድ ቤቱ ከተረጋገጠ፣ አሁን በግል የተደረገለት የትምህርት መቀበያ ቦታም ለልጁ ተስማሚ እንደሆነ ከታመነበት፣ የልጁ ALJ ወይም ፍርድ ቤቱ ወላጆች ለልጃቸው አዲሱ ምደባ ያወጡትን ወጪ ኤጀንሲው እንዲከፍል ሊያዝ ይችላል። ምንም እንኳን የሀገሪቱን የትምህርት ጥራት መለኪያዎች መሠረት በማድረግ በሕዝብ ድርጅቶች የሚቀርቡትን የትምህርት ጥራት መለኪያዎች የሚያሟሉ ባይሆኑም፣ በወላጆች የሚደረጉ የትምህርት ቤት ምደባዎች በ ALJ ወይም ፍርድ ቤት ዘንድ ተስማሚ እንደሆኑ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

# በወጪዎች ማካካሻ ላይ ገደብ፡

የወጪ ማካካሻ በ ALJ ወይም በፍርድ ቤት ሊቀነስ ወይም ሊከለከል የሚችለው፡

- ልጁ ከህዝብ ትምህርት ቤቱ ከመታገዱ ቀደም ብሎ በተደረገ ወላጆችም በተሳተፉበት የቅርብ ጊዜ የ IEP ቡድን ስብሰባ ላይ፣ ወላጆች እርምጃውን ለመውሰድ ያሳሰባቸውን/ያነሳሳቸውን ጉዳይና ልጁን በሕዝብ ወጪ በሚንቀሳቀስ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ለማስገባት የፈለጉበትን ምክንያት ጭምር በመዘርዘር፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ለልጁ የሚስማማ FAPE ለማሰናዳት ያቀረበውን ሐሳብ አለመቀበላቸውን ለ IEP ቡድኑ ያላሳወቁ ከሆነ፣ ወይም

- *ልጁ ከመንግሥት ትምህርት ቤት እንዲወጣ ከመደረጉ በፊት አሥር (10) የሥራ ቀናት (በዓል ሆነው የዋሉ የሥራ ቀናትንም ጀምሮ) ቀደም ብለው ወላጆች የልጃቸውን ሕዝባዊ ምደባ አስመልክቶ ያሳሰባቸውን ጉዳይ በማካተት ልጁን ከሕዝብ ትምህርት ቤት እንዲለቅ ለማድረግ ያነሳሳቸውን ሀሳብ በጽሁብ ለሕዝብ ኤጀንሲው ያላሳወቁ ከሆነ፣ ወይም*
- *ወላጆች ልጃቸውን ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከማስወጣታቸው ቀደም ብሎ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው አንድን ልጅ ለመገምገም ሲታሰብ ለወላጆች የሚሰጠውን የቀዳሚ ማስታወቂያ መርህ በመከተል (ተገቢና ተመጣጣኝ ነው ተብሎ የቀረበውን የግምገማ ዓላማ የሚያካትት መግለጫን በማከል) የሕዝብ ኤጀንሲው ለወላጆች የጽሑፍ ማስታወቂያውን በመስጠት አሳውቋቸው ከሆነ፣ ወይም*
- *ወላጆች የወሰዱት እርምጃ አሳማኝ ምክንያት የሌለው መሆኑ በዳኞች ምርመራ ከተረጋገጠ።*

*ከላይ የተዘረዘሩት የማስታወቂያ አስፈላጊነቶች እንዳሉ ሆነው፣ የወጪ ማካካሻ (ተመላሽ)፡*

- *ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ምክንያት ወላጆች የተባለውን ማስታወቂያ በወቅቱ ባለመስጠታቸው ብቻ ሊቀነስ ወይም ሊከለከል አይችልም፡*
    - *ወላጆች ማስታወቂያውን እንዳይሰጡ ትምህርት ቤቱ ከልክሏቸው ከሆነ፣*
    - *ከላይ በተገለጡት የIDEA የማስታወቂያ አስፈላጊነቶች መሠረት ወላጆች ምንም ምስታወቂያ ያልደረሳቸው ከሆነ፣*
    - *ከላይ የተጠቀሰው ማስታወቂያ ተከብሮ በተግባር ቢተረጎም፣ በልጁ ላይ ሊያስከትለው የሚችል የአካላዊ ጉዳት አዝማሚያ ተስተውሎ ከሆነ፣ እንደዚሁም*
- *ምናልባትም፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በማጤን ፍርድ ቤት ወይም ALJ በሚሰጠው አመዛዛኝ ውሳኔ መሠረት፣ ወላጆች የተባለውን ማስታወቂያ ባለማቅረባቸው የወጪ ማካካሻው ሊቀነስ ወይም ሊከለከል አይችልም ከተባለ፡-*
    - *ወላጆች ያልተማሩ ከሆኑ እና በእንግሊዝኛ መጻፍ የማይችሉ ከሆነ፣ ወይም*
    - *ከላይ የተጠቀሰው ማስታወቂያ ተከብሮ በተግባር ቢተረጎም፣ በልጁ ላይ ሊያስከትለው የሚችል የመንፈሳዊ ጉዳት አዝማሚያ ተስተውሎ ከሆነ።*

# የወላጅነት መብትን አካለ መጠን

## ለደረሱ ልጆች ማስተላለፍ

## IEP

## 34 CFR § 300.520

**በሜሪላንድ ውስጥ፣ በአንዳንድ በልዩ ሁኔታዎች ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ ልጆች ለአካለ-መጠን በደረሱ ጊዜ የወላጅ መብቶች ወደ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ ልጆች አይተላለፉም።**

*በሜሪላንድ ሕግ ሥር እንደተመለከተው፣ በ IDEA ሥር ለወላጆች የተሰጡት ሁሉም መብቶች፣ በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ አካለስንኩልናው ወዳለበት ልጃቸው ይተላለፋሉ። ተማሪው የአእምሮ ብቃት እንደሚጎድለው በስቴቱ ሕግ መሠረት ካልተረጋገጠበት እ ና የሚከተሉትን መጠይቆች የሚያረጋግጡ ሰነዶች ካሉ፣ ተማሪው 18 ዓመት ሲሞላው ነው፣ ይህ የመብት መተላለፍ የሚፈጸመው። ተጠናቅረው የተያዙ ሰነዶች የሚባሉትም፡*

- *ወላጆች ያልተገኙ ወይም ያልታወቁ እንደሆነና፣ ልጁም የወላጅ ምትክ ከሚመደብለት ይልቅ የወላጅነት መብቶች ወደሱ እንዲተላለፉለት የጠየቀበት ሰነድ ካለ፤*
- *ቀደም ባሉት ዓመታት፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ወላጆች በልጁ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ እንዲሳተፉ ወላጆችን በተደጋጋሚ ቢጠይቅም፣ ወላጆች ግን ያልተሳተፉ መሆናቸውን የሚያሳይ ሰነድ ካለ፤*
- *ወላጆች በልዩ ፍላጎት ትምህርት የውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ላይ ለመሳተፍ ዝግጁ አለመሆናቸውን ያረጋገጡበት ሰነድ ካለ፤*
- *ወላጆች በሕመም ምክንያት ለረጅም ጊዜ በሆስፒታል በመተኛታቸው፣ በማገገሚያ ሁኔታ ውስጥ በመሆናቸው፣ ወይም በብርቱ ሕመም/የጤና መታወክ ምክንያት፣ ከወላጆቹ አንዱ ወይም ሁለቱም የአቅም/የሰውነት መዳከም ውስጥ ያሉ በመሆኑ፣ ይህ መብት ከእንግዲህ ለልጁ እንዲተላለፍ በማለት ስምምነታቸውን የሰጡበት ሰነድ ካለ፤*
- *ወላጆች ከቁጥጥራቸው ውጪ የሆነ ልዩ ችግር ኢጋጥሟቸው በልዩ ፍላጎት ትምህርት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ለመሳተፍ ባለመቻላቸው፣ በዚህም የተነሳ የወላጅነት መብታቸው ወደ ልጃቸው እንዲተላለፍላቸው*

ስምምነታቸውን የሰጡ ለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሰነድ ካለ፤ ወይም

- ልጁ ከወላጆቹ ቤት ውጪ የሚኖር ከሆነና፣ በሌላ የሕዝብ ኤጀንሲ እንክብካቤ ሥር እንዳልሆነ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ካሉ፣ የሚሉት ናቸው።

ልጃቸው አብሯቸው የሚኖር የሆኑ የአካለስንኩል ተማሪ ወላጆች፣ ልጁ 18 ዓመት ሲሞላው የወላጅነት መብታቸውን ወደ ልጃቸው ለማስተላለፍ ባይስማሙና ልጁም የአእምሮ ብቃት ጉድለት እንዳለበት በስቴቱ ሕግ መሠረት ካልተረጋገጠበት በስተቀር፣ ከሁለቱ ወገኖች አንዳቸው ጉዳዩ በችሎት እንዲታይላቸው በማለት ማመልከቻውን ሊያስገቡ ይችላሉ።

አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ የፌዴራልና ስቴት ሕግጋት በሚደነግጉት መሠረት በወላጅ ምትክ ተወክሎ ከሆነ፣ የሕዝብ ኤጀንሲውም በፌዴራልና ስቴት ሕግጋት ሥር በታዘዘው መሠረት

የጽሑፍ ማስታወቂያ ለተማሪውና ለወላጅ ተተኪው ግለሰብ ነው የሚሰጠው። ሌሎች በ IDEA ሥር ለተተኪው የወላጅ ምትክ ሁሉም መብቶች፣ ተማሪው በክፍለ ግዛቱ ሕግ መሠረት የአእምሮ ብቃት እንደሚጎድለው ካልተረጋገጠበት በስተቀር እና ተማሪውም መብቶቹ ወደ እርሱ (ተማሪው) እንዲተላለፉለት ከጠየቀ፣ መብቶቹ ወደ ጠያቂው ተማሪ ይተላለፋሉ።

# አለመግባባቶችን ስለመፍታት

**IEP እና IFSP**

**34 CFR §§ 300.506-300.516 እና 34 CFR §§ 303.430-303-434 and §§ 303.440-303.449**

***የሚከተሉት ሥርዓታዊ አሠራሮች ብቁነትን ጨምሮ የአንድ ልጅን የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሀ-ግብርና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የተመለከቱ አለመግባባቶችን ስለመፍታት ለወላጆችና ለሕዝብ ድርጅቶች ይገልጻሉ። አማራጮቹ ግልግልን፣ የስቴት አቤቱታንና የፍትህ ሂደት አቤቱታን ያካትታሉ።***

## ግልግል፡

ግልግል የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጆች እና በ IDEA ክፍል B ስር ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ አለመግባባቶችን ለመቅረፍ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ከማቅረብ በፊት የሚነሱ ጉዳዮችን ጨምሮ፣ የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጆች እና የልጁ ትምህርትን በተመለከተ ኃላፊነት ያለበት የመንግስት ኤጀንሲ በማንኛውም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሂደት ነው።[25]የግልግል ዳኝነት በወላጆች ወይም በሕዝብ ድርጅቱ ሊጠየቅ ይችላል።[26]

በ IEP/IFSP ቡድን ስብሰባ ላይ፣ ወላጁ ስለ ልጁ IEP/IFSP ወይም ለልጁ ስለቀረበለት የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ካልተስማማ፣ የ IEP/IFSP ቡድኑ በግልጽ ቋንቋ ለወላጅ እነዚህን ማቅረብ አለበት፡

- በንግግር እና በጽሁፍ የተገለጸ የወላጅ ግልግል ዳኝነት የመጠየቅ መብት፤
- ስለስምምነት ሂደቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወላጁ መጠቀም የሚችለው የመገኛ መረጃ፣ ስልክ ቁጥርን ጨምሮ፤ እና
- ስለ ጥብቅና የማግኘት መረጃ እና ሌሎች በነጻ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ በቦታው የሚገኙ የህግ እና ተያያዥ አገልግሎቶች።

ወላጆች ስለ ግልግል ዳኝነት ያለው መረጃ ወደ ወላጆች የመጀመሪያ ቋንቋ እንዲተረጎም ሊጠይቁ ይችላሉ። በወላጆች የሚነገረው ቋንቋ በአካባቢው ካለው የትምህርት ስርዓት ባለው የተማሪው ብዛት ውስጥ ከ 1% በላይ የሚነገር ከሆነ፣ የ IEP/IFSP ቡድኑ ለወላጆቹ የተተረጎመውን ዶክመንት ከተጠየቀበት ቀን በ 30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት።

አንድ ስለ ግልግል ስልቶች/ቴክኒኮች ተገቢውን ሥልጠና የወሰደ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (OAH) ሰራተኛ የሆነ ሰው የግልግል ዳኝነት ሂደቱን ይመራል። OAH የ MSDE አካል ያልሆነ ገለልተኛ አካል ነው። OAH የግል ወይም የሙያዊ ግጭት የሌለባቸው ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ዝርዝር አለው፣ የልጁ ትምህርት ወይም እንክብካቤ ውስጥ ተሳታፊ የሆነ

[25] 34 CFR § 300.506(b)(1)(i).
[26] 34 CFR § 303.431(a).

የስቴት ኤጀንሲ ወይም የ LEA ሰራተኞች ያልሆኑ እና ግልግሉን ለማካሄድ በገለልተኛነት የተመረጡ። ብቃት ያለው ገላጋይ ከላይ እንደተገለፀው ገላጋይ ሆኖ ስለሚያገለግል ብቻ የ MSDE ወይም የ LEA ሰራተኛ አይሆንም።

- ግልግል ለወላጅ ወይም ለልጁ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም ትምህርት ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ኤጀንሲ፣ ግልግሉን ለማበረታታት ሲባል ከወላጆች ጋር ለተደረገ ግንኙነት የሚወጣውን ወጪም ጨምሮ ያለ ምንም ወጪ ይካሄዳል።
- የግልግል ጥያቄ የሚቀርበው ለልጁ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም ትምህርት ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ኤጀንሲና ለ OAH ነው። ወላጆች የግልግል ጥያቄ ሲሞሉ እርዳታ እንዲሆናቸው፣ ፎርም ከሕዝብ ኤጀንሲው ወይም ከ MSDE ዌብሳይት በ Www.marylandpublicschools.org. አድራሻ ማግኘት ይቻላል። በይበልጥ እርዳታ ለማግኘት የሕዝብ ኤጀንሲውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቢሮ ያናግሩ ወይም የ MSDE የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች/ልዩ ፍላጎት ትምህርት ክፍልን በስልክ ቁጥር 410-767-7770 ያናግሩ።
- በግልግሉ ወቅት ወላጆች ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው አማካሪዎች አብረዋቸው ሊኖሩና ሊያማክሯቸው ይችላሉ።
- የግልግል ጥያቄው በቀረበ በ 20 ቀናት ውስጥ ለወላጆችና ለሕዝብ ኤጀንሲው አመቺ በሆነ ቦታ እንዲካሄድ ይመቻቻል።[27]
- የግልግል ስብሰባዎች ዝግ ሂደቶች ናቸው። በግልግሉ ወቅት የሚካሄዱ ውይይቶች፣ በምስጢር የሚጠበቁ ሲሆን፣ በ IDEA ክፍል B ስር እርዳታ ለሚቀበል ማንኛውም የፌዴራል ወይም የስቴት ፍ/ቤት በቀጣይ ሂደት ለሚታይ ማንኛውም የፍትህ ሂደት ወይም የፍትሐብሔር ክስ በማስረጃነት ሊቀርቡ አይችሉም። ግልግሉ ከመጀመሩ በፊት ወላጆች ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው፣ ጉዳዩን በምስጢር መጠበቅ እንደሚገባቸው የሚያረጋግጥ መተማመኛ መፈረም ይኖርባቸዋል።
- በግልግሉ ውስጥ በነበሩ ወገኖች መካከል የተደረሰበት ስምምነት በጽሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይኸውም ይህንን ዓይነት ጉዳይ የመስማት ሥልጣን ባለው የስቴት ፍርድ ቤት ውስጥ ወይም የፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ በሕግ መከበር የሚችል ይሆናል። ይህ ስምምነት ኤጀንሲውን ማስገደድ በሚችል የኤጀንሲው ተወካይ እና ወላጅ መፈረም አለበት።
- አንድ ወላጅ የፍትህ ሂደት ችሎት ለመጠየቅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ አለመግባባቶችን ለመፍታት የግልግል ዳኝነት ይኖራል ነገር ግን አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ግልግሉን ተጠቅሞ የአንድን ወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ መብት መከልከል ወይም ማጓተት አይችልም።

## ግልግልን ለማበረታታት መገናኘት፡

የግልግል ሂደትን ላለመጠቀም የመረጡን ወላጆች፣ አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ለወላጆቹ በሚመች ሰዓትና ቦታ አግኝቶ የግልግልን ጥቅም ለማስረዳትና ወላጆች የግልግልን ሂደት እንዲጠቀሙ ለማበረታታት መሞከር ይችላል።

# በስቴት አቤቱታና በፍትህ ሂደት አቤቱታ መካከል ያለው ልዩነት፡

### ከግልግል በተጨማሪ፣ ወላጆች ከሕዝብ ኤጀንሲው ጋር የገጠማቸውን አለመግባባት ለመፍታት የስቴት አቤቱታ ሂደት ወይም የፍትህ አቤቱታ ሂደት የመጠቀም መብት አላቸው። እነዚህ አማራጮች ልዩ ሕጎችና ሥርዓት ሂደቶች አሏቸው።

የIDEA መተዳደሪያ ደንቦች ለስቴት አቤቱታዎችና ለፍትህ ሂደት አቤቱታዎች ልዩ ልዩ የሥርዓት ሂደቶች አሉት። ከዚህ በታች እንደተብራራው፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ኤጀንሲ አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ የ IDEAን ደንብ ጣሰ በሚልበት ጊዜ የስቴት አቤቱታ ማመልከቻ ማስገባት ይችላል። የአንድ ልጅ መለየትን፣ ግምገማን፣ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶችን ወይም አካል ጉዳተኛ የሆነን ልጅ ምደባን፣ ወይም የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርትን (FAPE) በተመለከተ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ ማስገባት የሚችሉት ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ ብቻ ናቸው።

የMSDE ባልደረባዎች ባብዛኛው የስቴት አቤቱታን መፍታት ያለባቸው፣ የጊዜ ገደቡ በተገቢ መንገድ ካልተራዘመ በስተቀር፣ በ 60 ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው። ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው የጊዜ መራዘም ጥያቄ ካላቀረቡ በስተቀር፣ አንድ ALJ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን በችሎት አዳምጦ

[27] 34 CFR § 303.431(b)(4).

(በአለመግባባት መፍቻ ስብሰባ ወይም በግልግል ካልተፈታ ማለት ነው) የችግር መፍቻ ጊዜው ባለቀ በ 45 የቀን መቁጠሪያ ቀን ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለበት።

የእነዚህን አማራጮች አጭር መግለጫና ማወዳደሪያ ለማየት እዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበውን ተያያዥ ሰነድ ይዩ።

# የስቴት አቤቱታ፡

## ከሌላ ስቴት የመጣን ጨምሮ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ጋር (MSDE) የስቴት አቤቱታ የማስገባት መብት አላቸው። ስቴቱ ምርመራ ማካሄድ እንዲችል ዘንድ፣ በጽሑፍ የቀረበው አቤቱታ የ IDEA መተዳደሪያ ደንቦችን በትክክል መከተል አለበት። MSDE የስቴት አቤቱታ አቀራረብ አሰራሮችን የወላጅ ስልጠና እና የመረጃ ማዕከላት፣ የጥበቃ እና ተሟጋች ኤጀንሲዎች፣ ገለልተኛ የኑሮ ማዕከላት እና ሌሎች ተገቢ አካላትን ጨምሮ ለወላጆች እና ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦች በስፋት የማሰራጨት ሃላፊነት አለበት።

ከሌላ ስቴት የመጣን ጨምሮ አንድ ግለሰብ ወይም ኤጀንሲ አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ደንብ በተመለከተ የፌዴራል ወይም የስቴት ሕግ ጥሷል ብሎ ካመነ ወይም ይኸው የሕዝብ ኤጀንሲ የፍትህ ሂደት ውሳኔ በሥራ ላይ አላወለም ብሎ ካመነ፣ የስቴት አቤቱታ ማስገባት ይችላል። የአቤቱታው ማመልከቻ MSDE ጋር መግባት ያለበት ሲሆን መላክ ያለበትም ለሚከተለው ነው፡ Assistant State Superintendent, Division of Early Intervention/Special Education Services, MSDE, 200 West Baltimore Street, Baltimore, Maryland 21201. ከ MSDE ጋር የስቴት አቤቱታ የሚያስገባው ግለሰብ ወይም ኤጀንሲ የአቤቱታውን ግልባጭ ለሕዝብ ኤጀንሲው በአንድ ጊዜ መላክ አለበት። አቤቱታ ማመልከቻውን ለማስገባት እንዲረዱ በዝርዝር የተጻፉ ሥርዓት ሂደቶችና ፎርም የ MSDE ዌብሳይት ላይ በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ በመሄድ ይገኛሉ፣ ወይም የክፍሉ የአቤቱታ ምርመራና የፍትህ ሂደት ቅርንጫፍ ጋር በስልክ ቁጥር 410-767-7770 በመደወል።

የስቴት አቤቱታው ማካተት ያለበት፡

- የህዝብ ኤጀንሲው የፌዴራል ወይም የስቴት ህግ ወይም ደንብ የሚጠይቀውን ነገር ጥሷል፣ ወይም የመንግስት ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት ችሎት ውሳኔን ተግባራዊ አለማድረጉን የሚገልጽ መግለጫ፤
- ይህ መግለጫ የተመሠረተበትን ተጨባጭ ነገሮች፤
- የስቴት አቤቱታውን የሚያስገባውን ግለሰብ/ኤጀንሲ ፊርማና የመገኛ መረጃ፤ እና
- የስቴት አቤቱታው ከአንድ የተወሰነ ልጅ ጋር የተያያዘ የሕግ መጣስ ከሆነ፡
    - የልጁ ስም እና የመኖሪያ አድራሻ፤
    - ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፤
    - ልጁ ወይም ወጣቱ ቤት አልባ ከሆነ፣ ሊገኝ የሚቻለውን መገናኛ ዘዴ እና ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፤
    - የልጁ ችግር ዓይነት ማብራሪያ፣ ከችግሩ ጋር የተያያዙ ተጨባጭ ነገሮችን ጨምሮ፤ እና
    - ለችግሩ መፍትሔ ተብሎ የቀረበውን፣ የስቴቱ አቤቱታ በገባበት ጊዜ አመልካቹ እስከሚያውቀውና ማግኘት እስከሚችለው ድረስ።

ማስታወሻ፡ የስቴት አቤቱታን ለማቅረብ ወላጆችን እና የህዝብ ኤጀንሲዎችን ለመርዳት MSDE ሞዴል ቅጾች አሉት። ወላጆች፣ የህዝብ ኤጀንሲዎች እና ሌሎች ወገኖች ሞዴል ቅጹን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ወይም ከላይ ያሉትን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ ማንኛውንም ሌላ ቅጽ ሊጠቀሙ ይችላሉ።

አንድ የስቴት አቤቱታ ተከስቷል የሚለው የሕግ መጣስ፣ አቤቱታው ስቴቱ ጋር ከመድረሱ ቀን እስከ አንድ ዓመት ቀድሞ ባለው ጊዜ ውስጥ የሆነ መሆን አለበት። MSDE የስቴት አቤቱታው በደረሰው በ 60 ቀን ውስጥ የእውነታ ግኝቶችን እና መደምደሚያዎችን የያዘ የጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለበት፣ የ 60 ቀን የጊዜ ገደቡን ማራዘም የሚችለው የሚከተለው ከሆነ ብቻ ነው፡

- አሁን የሚገኘውን አቤቱታ በተመለከተ ልዩ ሊጋጣሚዎች ካሉ፤[28] ወይም
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲ አለመግባባቱን ለመፍታት ግልግልን ወይም ሌሎች መንገዶች ለመሞከር ፈልገው የጊዜ ገደቡን በፈቃደኝነት ለማራዘም ከተስማሙ።[29]

ቢያንስ ቢያንስ MSDE የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፡

- አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ቦታው ላይ ገለልተኛ ምርመራ ማካሄድ፣
- አቤቱታ አቅራቢው፣ የስቴት አቤቱታ ውስጥ ስለ ክሶቹ ተጨማሪ መረጃ በቃል ወይም በጽሑፍ መስጠት እንዲችል ዕድል መስጠት፤
- ለሕዝብ ኤጀንሲው አቤቱታውን ለመፍታት የቀረበውን ሀሳብ እንዲያስገባ እና ተከራካሪ ወገኖች በ 34 CFR § 300.506 መሠረት በፈቃደኝነት በግልግል ዳኝነቱ እንዲሳተፉ እድል መስጠት[30]
- ከጉዳዩ ጋር የሚያያዘውን መረጃ ሁሉ ገምግሞ የሕዝብ ኤጀንሲው የፌዴራልና የስቴት ሕጎችን ስለመጣሱ ገለልተኛ ውሳኔ ማሳለፍ፤ እና
- ለአቤቱታ አቅራቢውና ለሕዝብ ኤጀንሲው አቤቱታ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ውንጀላዎች የሚመለከት እና የእውነታ ግኝቶችንና መደምደሚያዎችን፣ እንዲሁም የ MSDE የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን ምክንያት ያካተተ የጽሑፍ ውሳኔ መስጠት።

ውሳኔው የሚያስፈልግ ከሆነ የቴክኒክ ድጋፍ እንቅስቃሴዎችን፣ ድርድሮችን እና ተገዢነትን ለማሳካት የሚረዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ጨምሮ የመጨረሻ ውሳኔውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችንም ያጠቃልላል። MSDE አንድ የሕዝብ ኤጀንሲ ተገቢ አገልግሎችን ማቅረብ አልቻለም ብሎ ከወሰነ፣ በጽሑፍ የሚቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ የልጁን ፍላጎቶች ለማሟላት ተገቢ የሆነ የእርምት እርምጃ (ለምሳሌ፣ የማካካሻ አገልግሎቶች ወይም ምትክ የማካካሻ ገንዘብ መስጠትን የመሳሰሉ)፣ እና ለሁሉም የአካል ጉዳተኛ ልጆች ተገቢ የሆኑ የወደፊት አገልግሎቶችን ጨምሮ የሕዝብ ኤጀንሲው የከለከለውን ለልጁ ተገቢ የሆኑትን እነዚህን አገልግሎቶች እንዴት ማስተካከል እንደሚችል መግለጽ ይኖርበታል።

# የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት፡

ግልግል ወይም ሌሎች ኦፊሲዬላዊ ያልሆኑ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ እነሱን መጠቀምም የሚበረታታ ነው። ሁለቱ ወገኖች አቤቱታውን ከፈቱት፣ MSDE በፌዴራል ደንቦች መሠረት ምርመራ አያካሂድም።

# የፍትህ ሂደት አካል የሆነ የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት፡

MSDE የፍትህ ሂደት አካል የሆነ የስቴት አቤቱታ ቢደርሰው፣ ወይም አንድ የስቴት አቤቱታ በርካታ ችግሮች የያዘ ሆኖ ከእነዚህ አንዱ ወይም ብዙው የችሎት አካል ከሆኑ፣ MSDE የስቴት አቤቱታውን ማንኛውም የፍትህ ሂደት ውስጥ ያለውን ክፍል የፍትህ ሂደቱ እስከሚጠቃለል ድረስ ወደ ጎን ማስቀመጥ አለበት። ሆኖም የስቴት አቤቱታ ውስጥ ያለ ማንኛውም የፍትህ ሂደቱ ክፍል ያልሆነ ጉዳይ የጊዜ ገደቡና ከላይ የተጠቀሱትን የሥርዓት ሂደቶች ተከትሎ መፈታት አለበት። ከዚህ በፊት በፍትህ ሂደት ውሳኔ የተሰጠው ጉዳይ በስቴት አቤቱታ ውስጥ ቢነሳ፣ እና ይህ ጉዳይ እነዚሁኑ ወገኖች የሚመለከት ከሆነ፣ የችሎት ፍርዱ የሚያስገድድ ቃል ሲሆን፣ MSDEም አቤቱታ አቅራቢውን ይህንኑ መረጃ ይነግረዋል።

# የፍትህ ሂደት አቤቱታ፡

**አንድን ልጅ ከመለየት፣ ከግምገማ፣ ወይም ምደባ፣ ወይም የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ከማቅረብ ወይም ከትምህርታዊ ምደባ፣ ወይም ነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) ከማቅረብ ጋር ተያያዥ በሆነ ማንኛውም ጉዳይ ላይ የልጁ ወላጅ፣ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች አቅራቢ፣ የአካባቢው መሪ ኤጀንሲ፣ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ የፍትህ ሂደት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።[31]**

---

[28] 34 CFR § 300.152(b)(1)(i).
[29] 34 CFR § 300.152(b)(1)(ii).
[30] 34 CFR § 300.152(a)(3).
[31] 34 CFR § 303.440(a).

የፍትህ ሂደት አቤቱታው ተመሠረተበት የተባለው የደንብ ጥሰት ድርጊት የተከሰተው ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ካወቀ ወይም ማወቅ ከነበረበት ቀን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ስቴቱ በዚህ ክፍል ስር እንደዚህ ያለ የፍትህ ሂደት ችሎት ለመጠየቅ ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ ካለው በዚህ የስቴቱ ሕግ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ የተከሰተ መሆን አለበት።[32]

የሕዝብ ኤጀንሲው አውቆ በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ሳይፈቱ ተፈትተዋል ካለ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው በ IDEA ሥር ለወላጅ መስጠት የነበረበትን መረጃ ሳይሰጥ በመቅረቱ ምክንያት ወላጅ በጊዜ ገደብ ውስጥ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ እንዳያቀርብ ከተከለከለ ይህ የጊዜ ገደብ በዚህ ወላጅ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።[33]

የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ ለማስገባት፣ ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ (ወይም የወላጅ ጠበቃ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ጠበቃ) ለሌላው ወገንና ለ OAH የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማቅረብ አለበት። አቤቱታው ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሁሉ የያዘና በምስጢር የሚጠበቅ መሆን አለበት።

ወላጆች የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሲያስገቡ ለመርዳት የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም ልጃቸው ትምህርት ከሚከታተልበት፣ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች አቅራቢ ከሆነው የሕዝብ ኤጀንሲ ወይም ከ MSDE ድር ገጽ www.marylandpublicschools.org ማግኘት ይቻላል። ወላጅ በሚጠይቅ ጊዜ ወይም ወላጅ ወይም ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት አቤቱታ ካቀረቡ ስለማንኛውም ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ሊኖራቸው የሚችሉ የሕግ መርጃ ሀብቶች መረጃም ይገኛል። ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት የሕዝብ ኤጀንሲውን የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ቢሮ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቢሮ፣ ወይም የ MSDE የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ/የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍልን በስልክ ቁጥር (410) 767- 7770 ያናግሩ።

# የፍትህ ሂደቱ አቤቱታ ይዞታ፡

የፍትህ ሂደት አቤቱታው የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

- የልጁን ስም፤
- የልጁን የመኖሪያ አድራሻ (ወይም መኖሪያ ቤት የሌለው ልጅ ከሆነ፣ የተገኘውን የመገኛ መረጃ)፤
- ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፤
- ለልጁ ትምህርት ኃላፊነት ያለበትን የሕዝብ ኤጀንሲ ስም (ለምሳሌ፣ የአካባቢው የትምህርት ቤት ስርዓት)፣
- ከቀረበው ወይም እምቢ ከተባለው አነሳሽ ወይም ለውጥ ጋር የተያያዘ የልጁ ችግር ማብራሪያ፣ ከችግሩ ጋር የተያያዙ ተጨባጭ ነገሮችን ጨምሮ፣ እና
- ለችግሩ የቀረበውን መፍትሔ አቤቱታው በቀረበበት ጊዜ ለወገኑ እስከታወቀ ወይም እስከተገኘበት ድረስ።

ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ይህንን መረጃ የያዘ የፍትህ ሂደት አቤቱታ እስከሚያስገባ ድረስ ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው (ወይም የወላጁ ጠበቃ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ጠበቃ) የፍትህ ሂደት በችሎት ፊት ሊሰማለት አይችልም። የፍትህ ሂደት አቤቱታን ለማቅረብ ወላጆችን እና የህዝብ ኤጀንሲዎችን ለመርዳት MSDE ሞዴል ቅጾች አሉት። ወላጆች፣ የህዝብ ኤጀንሲዎች እና ሌሎች ወገኖች ሞዴል ቅጹን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ወይም ከላይ ያሉትን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ ማንኛውንም ሌላ ቅጽ ሊጠቀሙ ይችላሉ።

# ለፍትህ ሂደት አቤቱታው የሚሰጥ ምላሽ፡

አንድ ሰው ወይም ኤጀንሲ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሲያስገባ፣ ለልጁ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታና ትምህርት ኃላፊ የሆነው የሕዝብ ኤጀንሲ የሚከተሉትን ያደርጋል፡

- በነጻ ወይም በአነስተኛ ወጪ ማግኘት የሚቻሉትን የሕግ ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ለወላጅ ማስታወቅ፣

[32] 34 CFR § 300.511(e).
[33] 34 CFR § 300.511(f).

- የሥርዓት ከለላዎች ሰነድ ቅጂ ለወላጅ መስጠት፣ እና
- ግልግል ማድረግ እንደሚቻል ለወላጅ ማስታወቅ።

የሕዝብ ኤጀንሲው በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ ወላጅ ስላነሳቸው ጉዳዮች የሚናገር የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለወላጆች ካልላከ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ 10 ቀን ውስጥ የሚከተሉትን የያዘ መልስ የሕዝብ ኤጀንሲው ለወላጅ መላክ አለበት፡

- የሕዝብ ኤጀንሲው እርምጃ(ዎቹን) የመውሰድ ሃሳብ ለምን እንደሚያቀርብ ወይም እንደማይቀበል የሚገልጽ ማብራሪያ፣
- ሌላ ያጤናቸውን አማራጮችና እነዚህ አማራጮች ለምን እንደተተው የሚገልጽ ማብራሪያ፣
- ለቀረበው ወይም ሳይቀበለው ለቀረው እርምጃ መሠረት ሆነው ያገለገሉ የእያንዳንዱ የግምገማ ሂደት፣ ግምገማ፣ መዝገብ ወይም ሪፖርት መግለጫ፤
- ለቀረበው ወይም ሳይቀበለው ለቀረው እርምጃ አስፈላጊ እና መሠረት ሆነው ያገለገሉ ሌሎች ምክንያቶች መግለጫ፤
- የአካልስንኩል ወላጆች በሥርዓት ከለላዎች ሥር ጥበቃ እንዳላቸው የሚናገር መግለጫ እና፣ ይህ ማስታወቂያ ወደ መጀመሪያ ግምገማ መምሪያ ካልሆነ፣ የሥርዓት ከለላዎች ሰነድ ቅጂ የሚገኝበትን መንገድ፣ እና
- የ IDEAን ድንጋጌዎች ለመረዳት ወላጆች እርዳታ የሚያገኙባቸውን የመረጃ ምንጮች።

ይህ ምላሽ፣ በተገቢ ሁኔታ የሕዝብ ኤጀንሲው የወላጁ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ያልተሟላ ከሆነ ይህንን ከማለት የሚከለክል አይደለም።

የፍትህ ሂደት አቤቱታው ሌላው ወገን (ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ) ለሌላው ወገን በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች አንስቶ የሚያብራራ መልስ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ በ 10 ቀን ውስጥ መስጠት አለበት።

# የማስታወቂያ ብቃት፡

የፍትህ ሂደት አቤቱታ የሚደርሰው ወገን፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ መመዘኛዎችን አያሟላም በማለት መጥሪያ በደረሰው በ 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለOAH እና ለሌላኛው ወገን በጽሑፍ ካላስታወቀ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት የተጠየቀበት ማስታወቂያ በቂ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። የተባለውን ጉድለት በተመለከተ የቀረበው የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ አምስት (5) ቀናት ውስጥ OAH ቀደም ሲል የቀረበው የፍትህ ሂደት አቤቱታ መመዘኛዎችን የሚያሟላ እንደሆነ ይወስናል፣ ከዚያም ለሁለቱም ወገኖች በጽሑፍ ያሳውቃል።

አንድ ወገን፣ ሌላኛው ወገን ስምምነቱን በጽሑፍ ካረጋገጠለትና ከታች በተመለከቱት መሠረት ችግሩን በእርቅ ስብሰባ ተገናኝቶ ለመፍታት ዕድል ከተሰጠው፣ ወይም የፍትህ ሂደቱ ሲሰማ ከ አምስት (5) ቀናት ያልበለጠ ጊዜ ሲቀረው OAH የፈቀደ ከሆነ ብቻ፣ ለፍትህ ሂደት ያቀረበውን ጥያቄ ማሻሻል ይችላል። ለእርቅ ስብሰባውና ለፍትህ ሂደቱ የሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ የተሻሻለው የፍትህ መጠየቂያ ማስታወቂያ እንደገና ሰቀርብ ጀምሮ ይሆናል።

# በፍትህ ሂደቶች ጊዜ የልጁ ሁኔታ/ቦታ፡

አንድ በአስተዳደራዊ ወይም በፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይ ገና በመካሄድ ላይ ባለበት ወቅት (ስነ ምግባር ክፍል ሥር የተጠቀሱትን ሳይጨምር)፣ ወላጆችና የሕዝብ ኤጀንሲው በተቃራኒው እንዲሆን ካልተስማሙ በስተቀር፣ ልጁ አሁን ባለበት የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም የትምህርት ምደባ መቆየት ይኖርበታል። የፍትህ ሂደቱ ለቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች የመጀመሪያ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ ልጁ ክርክር ያልተነሳባቸውን አገልግሎቶች መቀበል አለበት፡፡[34] የፍትህ ሂደቱ ቀደም ብሎ ወደ ሕዝብ ትምህርት ቤት ለማስገባት የመጀመሪያ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ፣ ልጁ በወላጆች ስምምነት፣ ሁሉም የፍትህ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሕዝብ መርሀ ግብር ውስጥ መግባት ይኖርበታል። የALJው ውሳኔ፣ ወላጆች ለልጃቸው የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ ወይም የትምህርት ቦታ ለውጥ መደረጉ ተገቢ ነው ከሚሉት ጋር የሚስማማ ከሆነ፣ ተከታታይ የይግባኝ ጥያቄዎችም በሚስተናገዱበት ወቅት ሁሉ፣ ያ የትምህርት ምድብ ቦታ የተማሪው የወቅቱ ምድብ ቦታ ሆኖ ይቆያል።

ሆኖም ቅሬታው በዚህ ክፍል ስር ለመጀመሪያው አገልግሎት ከድንጋጌው ክፍል C (ISFP) ወደ ክፍል B (IEP) ከሚሸጋገር ልጅ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ እና ልጁ ሦስት ዓመት ስለሞላው ከአሁን በኋላ ለክፍል C አገልግሎቶች ብቁ ካልሆነ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው ልጁ ሲያገኝ የነበረውን የክፍል C አገልግሎቶች ማቅረብ አይጠበቅበትም። ልጁ በክፍል B ስር ለልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ወላጁ በ § 300.300(b) መሠረት የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሰጡ ከተስማማ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው በወላጅ እና በሕዝብ

(34) 34 CFR § 303.430(e)(2).

ኤጀንሲው መካከል ውዝግብ ያልተነሳባቸውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማቅረብ አለበት።[35]

# ችግሩን የመፍታት ሂደት፡

በወላጆች የቀረበው የፍትህ ሂደት ጥያቄ አቤቱታ በደረሰው በ 15 ቀናት ውስጥ፣ እንደዚሁም የፍትህ ሂደት ጥያቄው መታየት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው በወላጁ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ላይ ስለተገለጹት እውነታዎች ዝርዝር እውቀት አላቸው ከሚባሉት አግባብነት ካላቸው የግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ቡድን ወይም የግለሰባዊ ትምህርት መርሀ-ግብር (IEP) ቡድን አባል/አባላት ጋር በጋራ ስብሰባ ያደርጋል።

ስብሰባውም፡

- በሕዝብ ኤጀንሲው ስም ውሳኔ የማሳለፍ ሥልጣን ያለው የሕዝብ ኤጀንሲው ተወካይን ማካተት አለበት፤ እና
- ወላጁ ጠበቃ ካላመጣ በስተቀር የሕዝብ ኤጀንሲውን የሚወክል ጠበቃ ማካተት አይችልም።

ወላጁና የሕዝብ ኤጀንሲው ስብሰባው ላይ የሚገኙትን አግባብነት ያላቸውን የ IFSP ወይም IEP ቡድን አባሎች ይወስናሉ። የስብሰባው ዓላማ የሕዝብ ኤጀንሲው አለመግባባቱን የመፍታት ዕድል እንዲኖረው፣ ስለ ፍትህ ሂደት አቤቱታውና ለአቤቱታው መሰረት ስለሆኑ ተጨባጭ ነገሮች ወላጅ እንዲገልጽ ለማድረግ ነው።

የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባው አላስፈላጊ የሚሆነው፡

- ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲው ስብሰባውን ለመተው በጽሑፍ ሲስማሙ፣
- ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲው የግልግል ዳኝነትን ለመሞከር ሲስማሙ፣ ወይም
- የፍትህ ሂደት አቤቱታውን የጀመረው የሕዝብ ኤጀንሲው ከሆነ።

የሕዝብ ኤጀንሲው ወላጅ አጥጋቢ ሆኖ እስከሚያገኘው ድረስ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ (የችግር መፍቻ ወቅት) አቤቱታውን ካልፈታ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ ሊከናወን ይችላል።

ከዚህ በታች በ *ችግር መፍቻ 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ሰሌዳ ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች* ወይም *አፋጣኝ የጊዜ ሰሌዳዎች* በሚሉት ክፍሎች ወስጥ ከተጠቀሱት አጋጣሚዎች አንዱ ካልተከሰተ በስተቀር የመጨረሻ ውሳኔ መስጫው የ 45 ቀን የጊዜ ገደቡ የሚጀምረው የችግር መፍቻው 30 ቀን ካለቀ በኋላ ነው።

# የችግር መፍቻ የ 30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች፡

የችግር መፍታት ሂደቱን ለማራዘም ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲው ካልተስማሙ፣ የችግር መፍታት ሂደቱን ይቅር ብለው ካልተውት፣ ወይም ግልግል ካልተጠቀሙ በስተቀር፣ አንድ ወላጅ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባ ላይ አለመሳተፍ የችግር መፍታት ሂደቱንና የፍትህ ሂደት አቤቱታ የጊዜ ሰሌዳዎችን ስብሰባው እስከሚደረግ ድረስ ያዘገያል።

ተገቢ ጥረቶች አድርጎ፣ እነዚህንም ጥረቶች በሰነድ ከተያዙ በኋላ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው በመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባው ላይ ወላጆችን ተሳታፊ ለማድረግ ካልቻለ፣ የችግር መፍቻ ጊዜው ካለቀ ከ 30 ቀናት በኋላ የሕዝብ ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት አቤቱታው በ ALJ እንዲሰረዝ መጠየቅ ይችላል። የሕዝብ ኤጀንሲው ያደረጋቸው ጥረቶችን የያዘው ሰነድ፣ ለሁሉም ተስማሚ የሆነ የመገናኛ ሰዓትና ቦታ የሞከረበትን እንደሚከተሉት ዓይነት ሬኮርዶች ማካተት አለበት፡

- በስልክ ለማግኘት የተደወለባቸው ወይም የተሞከረባቸው ዝርዝር ሬኮርዶችና የስልክ ጥሪዎቹ ውጤቶች፤
- ለወላጅ የተላከ ማንኛውም ዓይነት ደብዳቤ ቅጂና ማንኛውም የተገኘ ምላሽ፤ እና
- ወደ ወላጆች ቤት ወይም መሥሪያ ቤት የተደረጉ ጉብኝቶችና ውጤቶቻቸው በዝርዝር ሬኮርዶች።

የሕዝብ ኤጀንሲው የመትሔ ስብሰባውን የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስታወቂያ በደረሰው በ 15 ቀናት ውስጥ ካላደረገ ወይም በመፍትሔ ስብሰባ ላይ ካልተሳተፈ፣ ወላጅ የፍትህ ሂደቱ ችሎቱ ተጀምሮ ውሳኔው በ 45 ቀናት ውስጥ እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

[35] 34 CFR § 300.518(c).

ወላጁና የሕዝብ ኤጀንሲው የመፍትሔ ስብሰባው እንዲቀር በጽሑፍ ከተስማሙ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ የ 45 ቀን የጊዜ ገደብ በማግስቱ ይጀምራል።

የግልግል ዳኝነት ወይም የመፍትሔ ስብሰባ ከተጀመረ በኋላ የችግር መፍቻው የ 30 ቀን የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት ወላጁና የሕዝብ ኤጀንሲው ምንም ስምምነት ሊኖር እንደማይችል በጽሑፍ ከተስማሙ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ የ 45 ቀን የጊዜ ገደብ በማግስቱ ይጀምራል።

ወላጁና የሕዝብ ኤጀንሲው የግልግል ዳኝነትን ለመሞከር ከተስማሙ፣ የችግር መፍቻው የ 30 ቀን የጊዜ ገደብ ሲያበቃ፣ ሁለቱም ወገኖች ስምምነት እስከሚደርሱ ድረስ የግልግል ዳኝነቱን ለመቀጠል በጽሑፍ መስማማት ይችላሉ። ሆኖም ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ከግልግሉ ትቶ ከወጣ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ የ 45 ቀን የጊዜ ገደብ በማግስቱ ይጀምራል።

# የችግሩን መፍትሔ ስምምነት፡

በመፍትሔ ስብሰባው ላይ ለውዝግቡ መፍትሔ ከተገኘለት፣ ወላጁና የሕዝብ ኤጀንሲው የሚከተለው ዓይነት በሕግ የሚያስገድድ ስምምነት ውስጥ መግባት አለባቸው፡[36]

- በወላጅ እና የሕዝብ ኤጀንሲው በስምምነቱ እንዲረጋ የሚያስችል ሥልጣን ያለው የሕዝብ ኤጀንሲው ተወካይ የተፈረመ፤ እና
- በማንኛውም ጉዳዩን ለመመልከት ብቁ የሆነ የስቴት ፍርድ ቤት (ይህንን ዓይነት ክስ ሊሰማ የሚችል የስቴት ፍርድ ቤት) ወይም የፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ።

በመፍትሔ ስብሰባው ምክንያት ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲው ስምምነት ላይ ቢደርሱ፣ ማንኛውም ወገን ስምምነቱን በሶስት (3) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያፈርሱት ይችላሉ።

# የፍትህ ሂደት ችሎት፡

በአለመግባባት ውስጥ ያለው ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በሚያቀርብበት ጊዜ፣ ወገን ያልያዘ የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት ዕድል አለው። ወላጅ ወይም የመንግሥት ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታ መሠረት የሆነውን ክስ በተመለከተ ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ካወቁበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፍትህ ሂደት ችሎቱን መጠየቅ አለባቸው። ለሁለቱ ዓመት መስፈርት ያሉት ብቸኛ ልዩ ሁኔታዎች፡ (1) LEA በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ሳይፈቱ ተፈትተዋል በማለቱ ምክንያት ወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ እንዳያቀርብ ከተከለከለ ወይም (2) LEA ለወላጅ መስጠት የነበረበትን መረጃ ሳይሰጥ በመቅረቱ ምክንያት ወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ እንዳያቀርብ ከተከለከለ።

# የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ)፡

- የ MSDE ሳይሆን፣ የአስተዳደራዊ ይግባኞች ቢሮ ተቀጣሪ ነው፤
- ከፍትህ ሂደቱ ዓላማ ጋር የሚጋጭ የግል ወይም የሙያ ጥቅም አይኖረውም፣
- ስለ IDEA ድንጋጌዎች፣ ከ IDEA ጋር የተያያዙ ፌደራልና የስቴት ደንቦችና የ IDEA ሕጋዊ ትርጓሜዎች የሚያውቅና የሚገነዘብ፣ እና
- ይግባኞችን የማስተዳደር፣ ውሳኔ የማድረግና የመጻፍ፣ ሁልጊዜ አንድ ዓይነትና ተገቢ የሆነ መደበኛ የሕግ አሠራር እውቀትና ችሎታ አለው።
- ችሎት ለማካሄድ ብቁ የሆነ ሰው፣ የችሎት መኮንን ሆኖ እንዲያገለግል በ MSDE ስለተከፈለው ብቻ የ MSDE ሰራተኛ አይሆንም።[37]
- MSDE የእነዚህን ሰዎች ብቃቶች መግለጫ ለማካተት የችሎት መኮንን ሆነው የሚያገለግሉ ሰዎችን ዝርዝር ይይዛል። ይህ መረጃ በ OAH ድርጣቢያ ላይ ይገኛል።[38]

---

(36) 34 CFR § 300.510(d).
(37) 34 CFR § 303.443(c)(2); 34 CFR § 300.511(c)(1-2).
(38) 34 CFR § 303.443(c)(3); 34 CFR § 300.511(c)(3).

# የፍትህ ሂደት አቤቱታ ርእስ፡

የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻውን የሚያስገባው የአቤቱታው ወገን (ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው)፣ ሌላው ወገን ካልተስማማ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው ላይ ያልተነሱ ጉዳዮችን ማንሳት አይችልም።

# የይግባኝ መብቶች፡

ማንኛውም በፍትህ ሂድቱ ተካፋይ የሚሆን ወገን (የIDEAን ሥርዓታዊ መንገዶች የሚመለከት ይግባኝን ጨምሮ) የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡

- በስቴት አስተዳደር አንቀጽ §9-1607.1 በተጠቀሰው የሜሪላንድ ኮድ መሠረት የፍትህ ሂደቶች ላይ ራስዎን መወከል ወይም ጠበቃ መያዝ፤
- በአማካሪዎችና የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ ልጆች ችግር ልዩ እውቀትና ሥልጠና ባላቸው ግለሰቦች መታጀብና ከነሱም ምክርን የማግኘት መብቶች፤
- ማስረጃን የማቅረብና የመከራከር፣ ምስክሮችም እንዲገኙና መስቀለኛ ጥያቄን የማቅረብ መብቶች፤
- የፍትህ ሂደቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ 5 የሥራ ቀናት በፊት ለተካፋይ ወገኖች ያልተገለጸ ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃን የመከልከል መብት፤
- የፍትህ ሂደቱን ሬኮርድ ቃል በቃል በጽሑፍ፣ ወይም በወላጁ ምርጫ፣ በኤሌክትሮኒክ ቅጂ የማግኘት መብት፤ እና
- በወላጆች ምርጫ፣ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የእውነታ ማጣራት ሂደቶችንና ውሳኔዎችን የማግኘት መብቶች።

# ተጨማሪ መረጃን ይፋ ማድረግ፡

የፍትህ ሂደት ይግባኝ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ አምስት (5) የሥራ ቀናት በፊት፣ እያንዳንዱ የሂደቱ ተካፋይ ወገን፣ ለሌሎቹ ሁሉም ተካፋይ ወገኖች ሁሉ፣ በዚያን ቀን የተጠናቀቁ ግምገማዎችንና በተካፋይ ወገኑ ግምገማ ላይ የተመሠረቱ ሆነው በፍትህ ሂደቱ ላይ ተካፋይ ወገኑ ሊጠቀምባቸው ያሰባቸውን አስተያየቶች ሁሉ ይገልጻል። አንደኛው ወገን ከሌላኛው ወገን ፈቃድ ሳያገኝ ግምገማዎችን ወይም አስተያየቶችን በፍትህ ሂደቱ ላይ ለማሰማት ቢፈልግ፣ ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ካላሟላ ALJው ሊያግደው ይችላል።

# የወላጅ መብቶች፡

ወላጁ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡

- ልጁ እንዲገኝ ማድረግ፤
- ይግባኙን ለሕዝብ ክፍት እንዲሆን ማድረግ፣ እና
- የይግባኙ ሬኮርድ፣ የተጨባጭ ነገሮች ግኝቶችና ውሳኔዎች በነጻ ለእርስዎ እንዲሰጡዎት ማድረግ።

# የይግባኝ ውሳኔ፡

አንድ ልጅ ነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) ማግኘቱን በተመለከተ የ ALJ ውሳኔ በተጨባጭ በተረጋገጠ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። የሥርዓታዊ ጥሰትን በሚመለከት ለሚቀርብ ያልተጣራ ክስ፣ አንድ ALJ፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሥርዓታዊ መጓደሎች በማጤን ብቻ አንድ ልጅ FAPE እንዳላገኘ ሊገነዘብ ይችላል፡

- ልጁን FAPE ከማግኘት መብቱ አደናቅፎት ከሆነ፤
- ልጁ FAPE እንዲያገኝ በሚደረገው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ወላጆች ለመካፈል ያላቸውን ዕድል በከፍተኛው አደናቅፎት ከሆነ፣ ወይም
- የትምህርት ጥቅም ከማግኘት ያስቀረ ከሆነ።

ከዚህ በላይ የተገለጹት ማናኛውም ድንጋጌዎች አንድ ALJ የሕዝብ ኤጀንሲው በፌዴራል ደንቦች IDEA (34 CFR 300.500 እስከ 300.536) በክፍል B ሥር ያሉት ሥርዓታዊ ከለላዎች ውስጥ ያሉ መስፈርቶች እንዲያከብር ከማዘዝ አይከለክሉትም።

አንድ ልጅ በተገቢው ተለይቶ ስለመታወቁ፣ ስለመገምገሙ ወይም ስለመመደቡ፣ ወይም ለልጁ በተገቢው ሁኔታ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች መሰጠታቸውን በተመለከተ የ ALJ ውሳኔ በተጨባጭ በተረጋገጡ ማስረጃዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። የሥርዓታዊ ጥሰትን በሚመለከት ለሚቀርብ ያልተጣራ ክስ፣ አንድ ALJ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሥርዓታዊ መጓደሎች በማጤን ብቻ አንድ ልጅ በተገቢው ተለይቶ ያለመታወቁን፣ ያለመገምገሙን ወይም ያለመመደቡን፣ ወይም ለልጁ በተገቢው ሁኔታ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ያለመሰጠታቸውን ሊገነዘብ ይችላል፡

- የልጁን በተገቢው ተለይቶ የመታወቅ፣ የመገምገም ወይም የመመደብ፣ ወይም የዚህን ልጅ እና የቤተሰቡን በተገቢው ሁኔታ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች የማግኘት መብት አስተጓጉሏል፤
- ልጁን መለየት፣ መገምገም ወይም መመደብ፣ ወይም ለዚህ ልጅ እና ለቤተሰቡ የቅድሚያ ጣልቃ ገብ እርዳታ አገልግሎቶች ማቅረብን አስመልክቶ በሚደረገው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ወላጆች ለመካፈል ያላቸውን ዕድል በከፍተኛው አደናቅፎት ከሆነ፤ ወይም
- የትምህርት ወይም የእድገት ጥቅም ከማግኘት ያስቀረ ከሆነ።

# ለብቻው የተለየ የፍትህ ሂደት አቤቱታ፡

የ IDEA የሥርዓታዊ መከላከያዎች ክፍል ውስጥ ወላጅን ከዚህ በፊት ካመለከተው የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጉዳይ ጋር ምንም የማይያያዝ ለብቻው የተለየ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ከማስገባት የሚከለክለው ምንም ነገር የለም።

# የጊዜ ሰሌዳዎችና የችሎት አመቺነት፡

የመፍትሔ ስብሰባዎች 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ገደብ ካለቀ በኋላ ካሉት 45 ቀናት ወይም ከዚህ በታች *የ 30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች፡* በሚለው ክፍል ውስጥ በተገለጸው መሰረት ከተስተካከለው የጊዜ ገደብ ካለቀ በኋላ ካሉት 45 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡

- በፍትህ ሂደት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ይደረሳል፤ እንዲሁም
- የውሳኔው ግልባጭ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ይላካል።

የትኛውም ወገን ጥያቄ በሚያቀርብ ጊዜ አንድ ALJ ከ 45 ቀናቱ የጊዜ ገደብ በላይ የተወሰኑ የጊዜ ማራዘሚያዎችን ሊሰጥ ይችላል። እያንዳንዱ ይግባኝ መደረግ ያለበት ለወላጁ ወይም ለልጁ አግባብ ባለው አመቺ ሰዓትና ቦታ መሆን አለበት።

# የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት (IEP ብቻ)፡

የሚቀጥሉትን በተመለከተ በአንድ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ስም የፍትህ ሂደት አቤቱታ በቀረበ ጊዜ፣ የሕዝብ ኤጀንሲው የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡

- በአሁኑ ጊዜ ትምህርት ቤት ያልተመዘገበ ወይም ትምህርት ቤት የማይሄድ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ፤
- የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ በመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት ቦታ በተመደበ ጊዜ፤ ወይም
- የባህሪ መገለጫዎች መወሰኛ ግምገማ።

የፍትህ ሂደት አቤቱታው በገባ በ 20 የትምህርት ቀናት ውስጥ የፍትህ ችሎቱ መካሄድ አለበት። ALJው ይግባኙ ካለቀ በኋላ በ 10 ቀን ውስጥ ውሳኔ ማድረግ አለበት። የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስታወቂያ በደረሰ በሰባት (7) ቀናት ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባ መደረግ አለበት፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ በ 15 ቀን ጊዜ ውስጥ ለሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ እስከሆነ ድረስ ካልተፈታ በስተቀር የፍትህ ሂደት ችሎቱ ይቀጥላል።

# የፍትህ ሂደት ችሎት ውሳኔ፡

ማንኛውም የግለሰባዊ መለያ መረጃን ከሰረዘ በኋላ የሕዝብ ኤጀንሲው ግኝቶቹን እና ውሳኔዎቹን ለስቴቱ አማካሪ ፓነል

የማስተላለፍ ሃላፊነት አለበት እንዲሁም እነዚህን ግኝቶች እና ውሳኔዎች ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት።[39]

## የፍርድ መጨረሻነት፡

ወላጆች ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ይግባኝ ካላሉ በስተቀር የ ALJ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። በግኝቶቹና በውሳኔዎቹ ይልተደሰተ ማንኛውም ወገን ይግባኙ ላይ የታየውን አቤቱታ በተመለከተ የማህበራዊ እርምጃ ሊያመጣ ይችላል።

## ይግባኝ፡

ማንኛውም የይግባኝ ወገን በንትርክ ላይ ያለው ጉዳይ መጠን ምንም ያክል ይሁን፣ በሜሪላንድ ሕግ መሠረት የመጨረሻው ውሳኔ በተሰጠ በ 120 ቀናት ውስጥ፣ በማንኛውም ተወዳዳሪ ሥልጣን ባለው የመንግሥት ፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ የወረዳ ፍርድ ቤት ለማህበራዊ እርምጃ ማመልከት ይችላሉ።
ለማንኛውም እርምጃ፣ ፍርድ ቤቱ፡

- የአስተዳደራዊ ሂደቶቹን ሪኮርዶች ማግኘት፤
- በወላጆች ወይም በህዝባዊ ኤጀንሲው ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ያዳምጣል፤
- ውሳኔውንም ሚዛን የሚደፋ ሆኖ በተገኘው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ይወስናል፣ እና
- ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ብያኔ ይሰጣል።

በ IDEA ክፍል B ውስጥ መብቶችን፣ ሥርዓታዊ ሂደቶችን፣ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ድንጋጌ 1990 (Americans with Disabilities Act of 1990, Title V of the Rehabilitation Act of 1973 [Section 504])፣ የ1973 የመልሶ ማቋቋሚያ/ማገገሚያ ድንጋጌ ርዕስ V (ክፍል 504)፣ ወይም የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች መብቶችን የሚጠብቁ ሌሎች የፌዴራላዊ ሕጎች መሠረት፣
በአሜሪካ ሕገ መንግሥት የተፈቀዱ የእርምት እርምጃዎችን የሚከለክል ወይም የሚገድብ አንዳችም ነገር የለም። በነዚህ ሕጎች ሥር እንዲሁም በ IDEA ክፍል B ስር የሚገኘውን እፎይታ ለማግኘት ለፍትሐብሄር ውሳኔ ከማመልከት በፊት፣ ወላጆች ወይም ሕዝባዊ ኤጀንሲው በ IDEA ክፍል B ስር ቢያመለክቱ ኖሮ ሊፈለግ የሚችለውን ማንኛውም የፍትህ ሂደት በሙሉ አሟጠው የጨረሱ መሆን የሚገባቸው ከሚሆን በስተቀር። ይህ ማለት በሌሎች ሕጎች ሥር ወላጆች በ IDEA ሥር የሚያገኙትን መፍትሔዎች ሊያገኙ ይችላሉ፣ ግን በነዛ ሕጎች ሥር መፍትሔ ለማግኘት ከፈለጉ፣ ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት ወላጆች መጀመሪያ በ IDEA ሥር የሚገኙትን አስተዳደራዊ መፍትሔዎች መጠቀም አለባቸው (ለምሳሌ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን፣ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባውን፣ እና ወገን ያልያዘ የፍትህ ሂደት ሥርዓቶች)።

# የጠበቆች ክፍያ

## <u>IEP እና IFSP</u> 34 C.F.R. § 300.517

በ IDEA ሥር በቀረበ ማንኛውም ክስ ወይም የፍትህ ሂደት ውስጥ፣ ፍርድ ቤቱ ተገቢ እንደሆኑ በሚወስነው መሰረት አሳማኝነት ያላቸው የጠበቃ ክፍያዎች ለሚከተሉት ሊሰጥ ይችላል፡

- የአንዱ ወገን የሆነው የአካለስንኩሉ ተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፤
- ቅሬታን ወይም በጣም አልባሌ፣ ምክንያት አልባ፣ ወይም መሠረተቢስ በሆኑ ማስረጃዎች ምክንያትነት ለተወሰዱ ተከታታይ እርምጃዎች ቅሬታቸውን ካስመዘገቡ ወላጆች በተቃራኒ ለሚቆመው ለወቅቱ ተጻራሪ ወገን፣ ማለት MSDE ወይም ማንኛውም ሌላ ሕዝባዊ ኤጀንሲ፤ ወይም
- የቀረበው ክስ አልባሌነት፣ ምክንያት አልባነት፣ ወይም መሠረተ ቢስነት ግልጽ ከሆነ በኋላም ክሱን ለሚቀጥል የወላጆች ጠበቃ፣ ወይም ከወላጆች ጠበቃ በተቃራኒ ለሚቆም ማንኛውም የወቅቱ ወገን ማለትም MSDE ወይም ሌላ የሕዝብ ኤጀንሲ፣ ወይም ከወላጅ በተጻራሪ፣ የወላጆች ቅሬታ ወይም የተከታታይ እርምጃዎች ምክንያት እንዲያው አግባብነት ለጎደለው ማንኛውም ዓላማ፣ ለምሳሌም ለማበሳጨት፣ አላስፈላጊ የጊዜ መጓተትን ለመፍጠር፣ ወይም አላግባብ የፍርድ ቤት ክስ ወጪን ለመጨመር በሚል አዝማሚያ ቀርቦ ከሆነ።

ለቀረቡ አገልግሎቶች ዓይነትና ጥራት የሚፈቀዱ ክፍያዎች፣ ድርጊቱ/እርምጃው በተነሳበት ማህበረሰብ የወቅቱ ስሌት ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል። ክፍያዎቹን በማስላት ጊዜ፣ ተጨማሪ ጉርሻ (ቦነስ) ማከል ወይም ብዜትን መጠቀም አይቻልም። በ IDEA ስር የሚገኙ ገንዘቦች FAPE ን ለማረጋገጥ በአንድ አካል ጉዳተኛ ልጅ ስም ከሚመጣ ውሳኔ ጋር

[39] 34 CFR § 300.513(d).

ተያያዥነት ያላቸውን የህግ ክፍያዎች፣ የፍርድ ቤት ወጪዎች ወይም ሌሎች ወጪዎችን ለመሸፈን ጥቅም ላይ አይውሉም።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ሥር ክፍያዎች ላይፈቀዱ ይችላሉ፡

- ለማንኛውም የIFSP ወይም የIEP ቡድን ስብሰባ፣ ስብሰባው የተጠራው በፍትህ ሂደቱ ውጤት ወይም በዳኝነት እርምጃው ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፤
- ለፍትህ ሂደት ማመልከቻ ከመግባቱ ቀደም ብሎ ለተደረገ ግልግል፣
- ለእርቅ/መግባቢያ ስብሰባዎች፤ እና
- በሚከተሉት ሁኔታዎች ሰበብ፣ ለወላጅ የጽሑፍ መግለጫ መሰጠቱን ተከትሎ ለቀረቡ አገልግሎቶች፡
    - የጽሑፍ መግለጫው እንዲሰጥ የተደረገው፣ በፌዴራላዊው የማሕበራዊ ሥነሥርዓት ደንቦች፣ የሥነሥርዓት ደንብ 68፣ ሥር በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከሆነ፣ ወይም በአስተዳደራዊ የጉዳይ ማጣራት ሂደት መሠረት፣ ጉዳዩ መታየት ከሚጀመርበት ከአሥር

      ቀናት በሆነ ጊዜ ቀደም ብሎ ከሆነ፤
    - የቀረበው አቅርቦት በአሥር ቀናት ውስጥ ተቀባይነት ካላገኘ፣ እና
    - ፍርድ ቤቱ፣ ጉዳዩ በተስተናገደበት ሂደት ላይ ወላጆች ያገኙት መፍትሄ ለወላጆች ከማሳረጊያ ስምምነት ላይ ከመድረስ የተሻለ ያልነበረ ሆኖ ካገኘው። ወላጁ የቀረበውን የማሳረጊያ ስምምነት ላለመቀበል እምቢ ማለቱ አሳማኝነት ካለው፣ ክፍያዎችና ወጪዎች ይፈቀዱለታል።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ክፍያዎች ሊቀነሱ <u>ይችላሉ</u>፡

- ወላጁ ወይም የወላጁ ጠበቃ ውዝግቡን ለመፍታት ከሚወሰደው ጊዜ በላይ ያለአግባብ ካጓተቱት፤
- የክፍያው መጠን፣ በወቅቱ ላይ ባለው፣ በአግባቡ ተመጣጣኝ ችሎታ፣ እውቅና እና የሙያ ልምድ ላላቸው ጠበቆች በማህበረሰቡ ውስጥ ለተመሳሳይ አገልግሎቶች ከሚፈቀደው የሰዓት ክፍያ ስሌት በላይ አላግባብ በልጦ ከተገኘ።
- ጉዳዩ የታየበት ባሕርይና ሁኔታ ሲጤን፣ የወሰደው ጊዜና የአገልግሎት መጠን በጣም የተንዛዛ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም
- የፍትህ ሂደት ጥያቄውን ሲያቀርብ፣ ጠበቃው ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን ያላቀረበ ከሆነ።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት፣ ክፍያዎች <u>አይቀነሱም</u>፡

- የሕዝብ ኤጀንሲው የመፍትሄ ሂደቱን ካራዘመው፣ ወይም
- በሥርዓታዊ መከላከያዎች መስፈርቶች ላይ ጥሰት ተፈጽሞ ነበር።

ወላጆች ለጠበቆቻቸው ያወጧቸውን ወጪዎቻቸውን መልሰው ለመቀበል የሚችሉት በ IDEA ውስጥ የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማሟላታቸው ላይ የሚመሠረት በመሆኑ፣ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ከጠበቆቻቸው ጋር መወያየት ይኖርባቸዋል።

## አባሪ፡

# የIDEA የአለመግባባት ፍቺ አሠራሮች ማወዳደሪያ ሠንጠረዥ

| | ግልግል | የፍትህ ሂደት አቤቱታ | አለመግባባት የመፍቻ መንገድ | የስቴት አቤቱታ |
|---|---|---|---|---|
| የሂደቱ አነሳሽ ማን ሊሆን ይችላል? | ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ፣ ለሁለቱም በፈቃደኝነት መሆን አለበት | ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ | ተከራካሪ ወገኖች ለማስቀረት ወይም ግልግልን ለመጠቀም ካልወሰኑ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው ጊዜ የሕዝብ ኤጀንሲው የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባውን ያዘጋጃል | ማኛውም ግለሰብ ወይም ኤጀንሲ፣ ከስቴት ውጪ ያሉትንም ጨምሮ |
| ማመልከቻ የማስገቢያ የጊዜ ግደቡ ምን ያክል ነው? | ምንም የተጠቀሰ የለም | ከመጠነኛ የሚጠበቁ ነገሮች ጋር አመልካች ወገን ስለችግሩ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከነበረበት ጊዜ በ 2 ዓመት ጊዜ ስጥ[1] | አንድ ወላጅ ባስገባው የፍትህ ጊደት አቤቱታ ምክንያት የሚወሰን | የሕግ ጥሰቱ ከተከሰተበት ቀን በኋላ እስከ 1 ዓመት ጊዜ ውስጥ |
| መፈታት የሚችሉት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? | በክፍል 300 ሥር ያለ ማንኛውም ጉዳይ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን ከማስገባት በፊት የተነሱ ጉዳዮችን ጨምሮ (ይህ የማይሆንባቸው ልዩ ጉዳዮች አሉ)[2] | መለየትን፣ ግምገማን ወይም የትምህርት ምደባን ወይም የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት አቅርቦትን የተመለከተ ማንኛውም ጉዳይ (ይህ የማይሆንባቸው ልዩ ጉዳዮች አሉ) | የወላጁ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ ከተነሱት ጉዳዮች ጋር አንድ ዓይነት | የ IDEA ክፍል B ወይም ክፍል 300 ተጥሰዋል የተባሉ ሕጎች |
| ጉዳዮቹን ለመፍታት የተሰጠው የጊዜ ገደብ ምን ያክል ነው? | ምንም የተጠቀሰ የለም | ለጊዜ ገደቡ የተወሰነ የጊዜ ማራዘም ካልተሰጠ በስተቀር፣ የጉድዩ መፍቻ የጊዜ ገደብ ካለቀ ከ 45 ቀናት በኋላ[3, 4] | ተከራካሪ ወገኖቹ ስብሰባውን ለመተው ወይም ግልግልን ለመጠቀም በጽሑፍ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የወላጆቹ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በደረሰ በ 15 ቀን ውስጥ የሕዝብ ኤጀንሲው የችግሩን መፍቻ ስብሰባ መጥራት አለበት<br><br>ተከራካሪ ወገኖቹ በተቃራኒው ካልተስማሙ ወይም ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው በችግር መፍቻ ስብሰባው ሳይሳተፍ ከቀረ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ 15 ቀን ውስጥ የችግር መፍቻ ስብሰባ ካልጠራ በስተቀር የችግር መፍቻ የጊዜ ገደብ የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ጊዜ ድረስ ውስጥ[3, 5, 6, 7] | የጊዜ ማራዘም ካልተፈቀደ በስተቀር፣ አቤቱታው ከደረሰ ከ 60 ቀናት በኋላ[8] |
| ጉዳዮቹን የሚፈታው ማነው? | ወላጅ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲ ከገላጋይ ጋር<br><br>ሂደቱ በፈቃደኝነት የሚሆን ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ለማንኛውም መፍትሔ መስማማት አለባቸው | የይግባኝ ባለሥልጣን/የአስተዳደር ህግ ዳኛ(ALJ) | ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲ<br><br>ሁለቱም ወገኖች ለማንኛውም መፍትሔ መስማማት አለባቸው | የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ[9] |

[1]በሚከተሉት ምክንያቶች ወላጁ የፍትህ ሂደት ከማስገባት ከተከለከለ የጊዜ ገደቡ ተፈፃሚ አይሆንም፡
(1) የፍትህ ሂደት አቤቱታ የገባበትን ምክንያት ችግሩ ተፈቷል ብሎ የሕዝብ ኤጀንሲው በግልጽ በሐሰት ከገለጸ፣ ወይም (2) የሕዝብ ኤጀንሲው በ

IDEA ክፍል 300 መሠረት ለወላጅ መሠጠት የነበረበትን መረጃ ካስቀረ (34 C.F.R. §300.511(f))።

[2]ይህ የማሆንባቸው ልዩ ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ የመጀመሪያ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ስምምነትን ወላጅ አልሰጥም ያለበትን ለመሻር የሕዝብ ኤጀንሲ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ወይም ግልግል መጠቀም አይችልም (34 C.F.R. §300.300(b)(3))፣ በወላጅ በኩል የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የተመደበን ወይም በቤት ውስጥ ትምህርት የሚማር ልጅን የመጀመሪያ ግምገማን ወይም ዳግም ግምገማንስምምነትን ወላጅ አልሰጥም ያለበትን ለመሻር የሕዝብ ኤጀንሲ የፍትህ ሂደት አቤቱታን ወይም ግልግልን መጠቀም አይችልም፤ (34 C.F.R. §300.300(c)(4)(i))፣ በወላጆች ምክንያት የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የተመደቡ ልጆች ወላጆች የፍትህ ሂደት አቤቱታ የማስገባት መብት ያላቸው የሕዝብ ኤጀንሲው የልጁን አስፈላጊ ነጥቦች በሚከተለው ሳያሟላ ሲቀር ብቻ ነው (34 C.F.R. §300.140)፤ የሕዝብ ኤጀንሲው ከፍተኛ ጥራት ያለው አስተማሪ ሳያቀርብ ቢቀር የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስገባት አይቻልም፣ ግን የስቴት ትምህርት ኤጀንሲ (SEA) ጋር የስቴት አቤቱታ ማስገባት ይቻላል (SEA) (34 C.F.R. §300.156(e))።

[3] በስነ ምግባር ሂደቶች ምክንያቶች የፍትህ ሂደት አቤቱታ ለአፋጣኝ የፍትህ ሂደት ችሎት ቢደረግ፣ ወይም ልጁ በወቅቱ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ ካልሆነ ወይም ትምህርት ቤት እየሄደ ካልሆነ፣ ችግሩን የመፍቻ የጊዜ ገደቡ 15 ቀናት ነው (ስብሰባው በ 7 ቀናት ውስጥ ተደርጎ)። ሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ ሆኖ እስካገኙት ድረስ ችግሩ ካልተፈታ፣ ይግባኙ ጥያቄው በቀረበ በ 20 ቀን ውስጥ መካሄድ አለበት፣ ውሳኔውም ይግባኙ ባለቀ በ 10 የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ መሰጠት አለበት (34 C.F.R. §300.532[c] እና COMAR 13A.05.01.15)።

[4] የይግባኝ ሰሚ መኮንን/ALJ ማንኛውም ወገን በጠየቀ ጊዜ የተወሰነ የጊዜ ማራዘም ሊሰጥ ይችላል። (34 C.F.R. §300.516(c))።

[5] ደንቦቹ ለመፍትሔ ለተሰጠው የ 30 ቀን የጊዜ ገደብ ማስተካከያ እንዲደረግ ይፈቅዳሉ። የፍትህ ሂደት የ 45 ቀን የጊዜ ገደብ የሚጀምረው የሚከተሉት ሁኔታዎች ከሆኑ ከአንድ ቀን በኋላ ነው፡ (1) ሁለቱም ወገኖች የመፍትሔ ስብሰባውን ለመተው በጽሑፍ ይስማማሉ፣ (2) የግልግል ወይም የችግር መፍቻ ስብሰባው ከጀመረ በኋላ ግን የ 30 ቀን የጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት፣ ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ ሊደረስ እንደማይቻል በጽሑፍ ከተስማሙ፣ (3) የ 30 ቀን የችግር መፍቻ ጊዜ ገደቡ ካለቀ በኋላ ግልግሉን ለመቀጠል ሁለቱ ወገኖች በጽሑፍ ተስማምተው፣ በኋላ ግን ወላጁ ወይም የሕዝብ ኤጀንሲው ከግልግል ሂደቱ ለቅቆ ሲወጣ። (34 C.F.R. §300.510 (c))።

[6] ወላጅ በመፍትሔ ስብሰባው ላይ መሳተፍ ያለመቻል ስብሰባው እስከሚደረግ ድረስ የመፍትሔውን ሂደትና የፍትህ ሂደት ችሎቱን የጊዜ ገደቦች ያጓትታል። (34 C.F.R. §300.510(b)(3))።

[7] የሕዝብ ኤጀንሲው የመፍትሔ ማግኛ ስብሰባውን የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በደረሰው በ 15 ቀናት ውስጥ ሳያደርግ ከቀረ ወይም የመፍትሔ ስብሰባ ውስጥ ሳይሳተፍ ከቀረ፣ የፍትህ ሂደት ይግባኙን የጊዜ ገደብ ለመጀመር ወላጅ የALJን ጣልቃ ገብነት ሊጠይቅ ይችላል (34 C.F.R. §300.510(b)(5))።

[8] አንድ የተወሰነ አቤቱታን በተመለከተ ልዩ ሁኔታዎች ከተከሰቱ የስቴት አቤቱታውን የመፍቻ የጊዜ ገደቡ ሊራዘም ይችላል፣ ወይም ወላጁ (ወይም ግለሰቡ ወይም ኤጀንሲው፣ ግልግል ወይም ሌላ የችግር መፍቻ መንገድ በስቴት ድንጋጌዎች ሥር ለግለሰብ ወይም ለኤጀንሲ የሚገኝ ከሆነ) እና የሕዝብ ኤጀንሲው ግልግል ለመጠቀም ወይም በስቴቱ ድንጋጌ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ሌላ የችግር መፍቻ ዘዴ ለመጠቀም ከተስማማ (34 C.F.R. §300.152(b)(1))።

[9] የ MSDE የአቤቱታ ሂደቶች የሕዝብ ኤጀንሲው ለአቤቱታ መልስ የሚሰጥበትን ዕድል፣ በሕዝብ ኤጀንሲው ምርጫ፣ አቤቱታውን ለመፍቻ የመትሔ አቅርቦት፣ እና አቤቱታ ያቀረበው ወላጅና የሕዝብ ኤጀንሲው በፈቃደኝነት ግልግል ለማድረግ እንዲስማሙ ዕድል ይሰጣሉ። (34 C.F.R. §300.152(a)(3))። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ አቤቱታ አቅራቢውና የሕዝብ ኤጀንሲው ችግሩን ለመፍታት MSDE ሳይጠቀሙ አለመግባባቱን ሊፈቱ ይችላሉ።

Maryland State Department of Education
Division of Early Intervention & Special Education Services
200 West Baltimore Street
Baltimore, Maryland 21201
410-767-0249 (ስልክ)
410-333-1571 (ፋክስ)
http://www.marylandpublicschools.org